# ትግላችን ዜና

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘ.

Prepared by the Ethiopian Students Union
in Europe

P.O.Box 3198 10364 Stockholm 3 SWEDEN


# በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ፲፰ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ራፖርና የፖለቲካ ውሳኔ


Vol. 6 No. 1
September 1978

ቅጽ ፮ ቁጥር ፩
መስከረም ፲፱፻፸፩

# በአኢተማ 18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት

በአውሮፓ የኢት ተማሪዎች ማህበር 18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ በበርሊን ከተማ ከጁላይ 31–ኦገስት 7. ድረስ ታላቅ የትግል መንፈስና ቆራጥነት በተሞላበት መንገድ ተካሂዷል::

የ18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ከኢት ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ ሲታይ ከመቸውም ጊዜ ከተደረጉት ስብሰባዎች ጠንካራና ታሪካዊ ሆኖ ተገኝቷል:: ነገሮች የታሪክ አዶገታቸውን ተከትለው ወደፊት ሲያመሩ በአውሮፓ የኢት ተማሪዎች ማህበርም በዚያው መጠን እየበሰለ አብዮታዊ ልምዶችን አያከማቸ ማደጉን በርግጥ አስመስክራል::

የ18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ በሚካሄድበት ወቅት አብዮታችንና አገራችን ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ መግባታቸውን ጉባኤው በደንብ በመረዳት በታላቅ ትእግሥት የኢት ሁኔታ አጥንቶ ትክክለኛ አቋም ወስደበታል::

በአውሮፓ የኢት ተማሪዎች ማህበር ለአያሌ አመታት ደግሞ ደጋግሞ ለኢት ጭቁኖች የገባውን ''ለነፃ፣ ለተደራጀና ለታጠቀ የህዝብ ትግል'' የሚለውን መፈክር አሁንም አንግቦ፣ ታጋይ ሃቀኛና የህዝብ ወገኖች በአድሃሪ ጥይት ተመተው የጣሉትን አርማ አንስቶ፣ አብዮቱን ከግቡ ለማድረስ በግፍ የፈሰሰው ንፁህ ደማቸውን በአኩሪ ታሪክ ለማደስና አዲሲቷን ኢት ለመገንባት በአንድ ቃል ድምፁን ያሰማበት ጉባኤ ነበር::

## መ ግ ቢ ያ

የኢት አብዮት ከፈነዳበት 1966 ዓ.ም ጀምሮ ቁጥራቸው በርከት ባሉ ውጥረቶች ውስጥ አልፏል:: እነዚህ ውጥረቶች በፈነዱበት ወቅት የኢት ህዝቦች ትግል መጠነኛ እምርታ እያገኘና በአጥቂነትና በተከላካይነት እየተፈራረቀ እነሆ እስከአለንበት ወቅት ደርሷል:: በአጥቂነትና በተከላካይነት እንዲለዋወጥ የውጭና የውስጥ ፀረ–አብዮት ኃይሎች ታላቅ ሚና ተጫውተዋል::

ከውጭ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በሽህ ድር በተወሳሰበ ወጥመድ አብዮታችንን ለመቅጠፍ በከፍተኛ ደረጃ ተፈታትኗል:: ዛሬም እየተፈታተነ ነው:: ኃያላን መንግሥታት ዓለምን ቆራርሶ በመዳፋቸው ሥር ለማድረግ በሚያደርጉት ሽኩቻ ዘንድሮ

''የአፍሪካ ቀንድ''በሚለው ችግር አያሌ ጭቆኖች ደማቸውን አፍስሰዋል:: ለአገራችን ብሔራዊ ነፃነትና ክብር ህይወታቸውን የሰጡት ጭቆኖች ቶጥራቸው አጅግ ከፍተኛ ሆኖ አናገኘዋለን::

በውስጥ ከአምናው ጉባኤችን በፊት ጀምሮ በተከሳካይነት የሚገኘው አብዮታችን ዛሬም በተከሳካይነት ተውስኖ ይገኛል:: ከዚህ በተረፈ ያለፉት ጉባኤያቻችን የማያወላውል ድጋፋቸውን የሰጡት መኢሶን ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ጠንክሮና የትግል ስልቱን ለውጦ ከኢት ጭቆኖች ጉን በመሰለፍ ከዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ጋር ወደፊት በመራመድ ያነገበውን ለነፃ፣ ለታደረጀና ለታጠቀ የህዝቦች ትግል የሚለውን መፈክር ያለአንዳች ጣልቃ ገብ ከሥራ ላይ አያዋለና ለዘላቂውም ትግል ጥርጊያ መንገድ አየከፈተ ይገኛል::

ይህ ጉባኤ በሚካሄድበት በዛሬው ወቅት ''ኢህአፖ'' የዛሬ ሁለትና አንድ ዓመት የነበረውን የሟሟጠጧ የፖለቲካ ጠቀታውን ዘጧውቶ ዛሬ ከኢት ህዝቦች የትግል ታሪክ ውስጥ ተተፍቶ የወጣበት ወቅት ነው:: ከዚህ በተረፈ ግን በተለይ በዛሬው ወቅት በታላቅ ትንቅንቅ ውስጥ የሚገኘውን አብዮት ቀልበስ በአንድ ተልካሸና ከሳይ በዘጧነ የንዑስ ከበርቴ ፖርቲ ለመተካት አድሃሪያን ''የወዝ አደሩን ድርጅት'' ስም ለማጉደፍ ሽር ጉድ የሚሉበት ወቅት ነው::

ይህን ጉባኤ በምናደርገበት ጊዜ ታሪክ አራሱን በአገራችን በመድገም በሌሎች አውነተኛ አብዮት በተካሄደባቸው አገሮች የታየው የቀኝ አድርባይ ዛሬ በአገሪቱ አብዮቱ አንገብ ያንፈረጠጠበት ወቅት ነው:: በአውሮፖ የኢት ተማሪዎች ማህበር ባለፉት አመታት የገራ አድርባዮችን ሸንጡን ገትሮ ታገሎ የፖለቲካ ከስረታቸውን በገሃዱ አጋልጦ የአብዮቱን ሰፈር ባፀዳበት ጊዜ አንድ ሌላ ከፍተኛ ዞር፣አንድ ሌላ አብዮታዊ ፅዳት ከቀኝ አድርባዮች ጋር እንደሚጠብቀው ምንም ምትሀት/ኢሉዢን/ አልነበረውም::

የዛሬው ትግል ከቀኝ አድርባዮች ጋር እንደሆነ ፍጹም ገልጽ ነው:: ሌላ አማራጭ፣ሌላ አቋራጭ፣ሌላ ሶስተኛ መንገድ የለም:: ያለው ወይ ለነፃ፣ ለተደራጀና ለታጠቀ የህዝቦች አመጽ ቆሞ ከዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር ወደፊት መጓዝ፣ ወይም ከነፃ፣ ከተደራጀና ከታጠቀ የህዝቦች አመጽ በፊት /በአቋራጭ/ ሥልጣን ነው::



ማህበራችን የመጀመሪያውን አማራጭ መርጦ ትግል ከጀመረ በርከት ያሉ ዓመታት ስለአለፉት የዛሬው ወቅት ይህ ቃል ኪዳን ማደሸና በተግባር መመንዘሪያ መሆኑን በተደጋጋሚ ያረጋገጣል::

የኢት አብዮት ከመጋቢት ወር 1969.ዓ.ም በአስገራሚ ፍጥነት ወደ ተከሳካይነት አያሽቆለቆለ ከሄደበት ወቅት ጀምሮ ሁኔታው በዚያው መጠን አየተበላሸ ሄዷል:: ለተራማጆች መጠነኛ ቢሆንም አመቺ የነበረው ህጋዊ መንገድ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ጠበበ:: ከዚህም በመነሳት ሃቀኛ ተራማጆች አደጋውን ጠቁመው ነበር:: ይህም ፍጹም አደማጭ በማጣቱና ደርገ ከተራማጆች ወገን የቢሮክራሲው ጉያ አየሞቀው ስለሄደ መኢሶን የትግል ሥልት እንዲለውጥ አስገድዶታል:: ከዚህም የትግል ሥልት ለውጥ በኋላ በአገሪቱ ላይ ትልቅ ትርምስ፣የንዑስ ከበርቴ አእምሮ ጭንቀትና የኢኮኖሚ ውድቀት ከመቸውም ጊዜ ጉልተው ታይተዋል::

ከዚህ ወቅት በኋላ በቲዎሪ በቻ ይነገር የነበረው ልዩ ልዩ የትግል ዘዴዎችን ማቀነባበር በተግባር መዋል ጀመረ:: በኢት አብዮት ውስጥ አንድ የታሪክ መድረክ ተከፈተ:: ጊዜው አየጠመረ ሲሄድአንክርዳዱ ከስንዴው በመለየቱ የኢማሌድህ ገጽ በገሃድ መታየት ጀመረ:: ወዝና፣ ማሌሪድ በገሃድ አድርባይነታቸው አየታየ ሄደ:: በአጠቃላይ ከ17ኛው ጉባኤችን ወዲህ የአገሪቱ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የሶሻል ሁኔታ በየቀኑ አሳሳቢ ደረጃ በመድረሱ ሃቀኛ ተራማጆች ወደ ህዝብ ወገን አድሃሪያን በፀረ—ህዝብ ወገን እንደተሰበሰቡ በአውን ታየ::

ይህም በዝብጥ ሊታይ የቻለው አድርባይ ድርጅቶች ተቀብለው የነበሩትን የዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን አየከዱ፣ ሃቀኞች አሱን በስራ ለመተርጉም በአደረጉትና በሚያደርጉት ጥረት ነበር:: በዚህ ብቻ ሳይወሰን በዛሬው አዲሱ ቀኝ ኃይልና በሃቀኛ ተራማጆች መካከል ያለው ልዩነት ብሔራዊ ነፃነቱን ሳለማስደፈርና አድርባዮች ለተከተሉት ስህተተኛ አርምጃ፣ማለትም የውጭ አርዳታን አንደወሰኙ፣ የህዝቦችን ትግል አንደአደጋዥ የሚለውን የአብዮት ወሰኙና አብዮቱ ከገባበት ውጥረትና ውድቀት ያለው መውጫ የህዝቦች የመፍጠር ችሎታ ራስን በራስ የመተማመን መርህ ማድረግ አንጂ አርዳታን በወሳኝ ደረጃ ማስቀመጥ አለመሆኑ ለአዲሱ ቀኝና በሃቀኛ ተራማጆች መካከል ልዩነት ፈጠረ::

በዚህ ብቻ ሳይወሰን የአገሪቱ ሁኔታ በአጠቃላይ ልዩ መልክ እየያዘ ሄዷል፡፡ በሰሜን ኢት በተለይም በኤርትራ ለችግሩ በቂ መፍትሔ አልተወሰደም፡፡ ወታደራዊ እርምጃ ብቻ ለችግሩ ምንም መፍትሔ ስለማይሰጠው አሁንም ቢሆን ዘላቂና ዋስትና ያለው መፍትሔ ዲሞክራሲያዊ ውይይት መሆኑን ደርግ የተረዳው አይመስልም፡፡ በዚህ በሰሜን አካባቢ ይንፈራገጥ የነበረው ኢዲህ መናኸሪያውን ከሎንደን ወደ ከርቱም በማዛወር ለአድሃሪ ትግሉ አዲሚ ሲጠምር አሁንም ይፈራገጣል፡፡

በመሃል አገር ያለው ሁኔታ እጅግ አሳዛኝ እየሆነ ሄዷል፡፡ በመሃል አገር የሰፈረው ቢሮክራሲና አድርባይ ድርጅቶች በአንድ ላይ በማበር በተራማጆችና በጭቁኑ ላይ ይህ ነው የማይባል በደል እየፈጸሙ ናቸው፡፡ ያለውን እሥር ቤት በወዝ አደር፣ በገበሬ፣ በመለዮ ለባሽ፣ በአብዮታዊ ምሁርና በወጣቱ ከሞላ በኋላ የቀበሌውንም መሥሪያ ቤት ወደእዚሁ አርኩስ ሥራቸው አዘውረውታል፡፡ በአጠቃላይ መሃል አገርን የአብዮቱ ደጀን ከማድረግ የአገር ወዳድ፣ የዲሞክራቱና የተራማጅ እሥር ቤት አድርገውታል፡፡

በደቡብ ምሥራቅና በምሥራቅ ያለው ሁኔታም ከዚህ ቢብስ እንጂ ፍጹም አይሻልም፡፡ በሶማሌና በኢት መካከል የተነሳው ጦርነት መነሻው የሶማሌ ገዥ መደብ ተስፋፊነት ቢሆንም በቀጥታ ለጣልቃ ገብነት ያገለገለው በአገሪቱ ውስጥ የነበረውና ያልተፈታው የብሔረሰብ ጥያቄ ነው፡፡ በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ የሚገኙ ጭቁን ብሔረሰቦች አንዴ በሶማሌ ሰበብ፣ አንዴ ጭቆናቸውን ለማቋቋም በመደራጀታቸው እየታጠፉ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ አገሪቱ በትልቅ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ሰምጣ ትገኛለች፡፡ ከዚህ ከፖለቲካ ቀውስጥ ለመውጣት ያለው ዋና አማራጭ አንድ ብቻ ነው፡፡ እሱም የጭቁኖችን የዲሞክራሲ መብት ያለገደብ አምኖ ተቀብሎ መልቀቅ ነው፡፡

የአገሪቱን የኢኮኖሚ ድቀት በምንመለከት ጊዜ ከመቸውም የበለጠ ያስደነግጣል፡፡ ከ73-የማያንስ ችግር በኢት ገብቷል፡፡ በገጠር፣ ለገጠር ነዋሪዎች የሚያስፈልጉ ሸቀጦች ዋጋ ከመጠመራቸው ሌላ በፈለገው ዋጋም አይገኝም፡፡ እንኳ ሌላ ቀርቶ ጨውና ዘይት ዘሬ የትየለሌ ሆነዋል፡፡ በከተማ የሸቀጥ ቀርቶ የእለት ምግብ አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ የዳቦ ሰልፍ ጠምሯል፡፡ ከእንጠት አቅም ገዷል፡፡ ይህን ዓይነት የኢኮኖሚ ድቀት ሊፈታ የሚችለው በዲሞክራሲያዊ መንገድ ሊሠራ



የሚችል ያው በህዝቡ የመፍጠር ችሎታ ላይ የተመሠረተ፣ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ልምድ ላይ በተመሠረተ እድገት እንጂ ከሰማይ በታች ያለ ምንም ድጎማ ሊረዳው አይችልም፡፡

## የ18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ አካሄድ

በበርሊን ከተማ በተካሄደው 18ኛው በአውሮፓ የኢት ተማሪዎች ጉባኤ ላይ የተገኙ ቅርንጫፍ ማህበራት 15 ናቸው፡፡ ከእነዚህ ቅርንጫፍ ማህበራትና ከሌሎችም ማህበራችን ከሚደገፉ እህት የኢት ተማሪዎች ጥናት ክበባት፣ የውይይት ቡድኖች እንዲሁም በግለ ሰብ ደረጃ በጠቅላላው በጉባኤው ላይ ከ180 በላይ ተካፋዮች ተገኝተዋል፡፡ የዘንድሮውን ጉባኤ ልዩ የሚያደርገው አንድ ነጥብ ቢኖር ከዚህ ከጉባኤው ቀን በፊት ዓለም አቀፍ የኢት ተማሪዎች ማህበራት ህብረት ለማጠናከርና ለ18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ የኢት ተማሪዎች ከእስያ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከሰሜን አሜሪካ ወኪሎች በመገኘት ለጉባኤው ልዩ ክብደት ሰጥተውታል፡፡

በጉባኤው የተገኙ የአኢተማ ቅርንጫፍ ማህበራት የሚከተሉት ነበሩ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1- ቤልጅም | 6- ኖርዌይ | 11- ዩጎዝላቪያ |
| 2- ፊንላንድ | 7- ስዊድን | 12- ችኮዝላቫኪያ |
| 3- ቡልጋሪያ | 8- ሃንጋሪ | 13- ሶቪየት ህብረት |
| 4- እንግሊዝ | 9- ስዊስ | 14- ምእራብ ጀርመን |
| 5. ፈረንሳይ | 10- ሩማንያ | 15- ምስራቅ ጀርመን |

በጉባኤው በአካል ተገኝተው የትግል አንድነት መግለጫ የሰጡና የተሳተፉ የኢት ተማሪዎች ወኪሎች፡፡

1- በአሜሪካ የተባበሩት ኢት ተማሪዎች አንድነት ማህበር (UPESUNA)
2- በአሜሪካ አዲሱ የኢት ተማሪዎች ንቅናቄ (NESMNA)
3- በቻይና የኢት ተማሪዎች ማህበር
4- በእስራኤል የኢት ተማሪዎች
5- በኔዘርላንድ የኢት ተማሪዎች

በቻላይ 30–31 ዓለም አቀፍ የኢት ተማሪዎች ማህበራት ህብረት ህገ ማህበር የማጽደቅ ውይይት በልዩ ልዩ እህት የአህጉር ማህበራት መካከል ተጀመረ፡፡

በቻሳይ 31 ማታ የአኢተማ ሥራ አስከያጅ፣ የአኢተማ የመጽሔት ቦርድ፣ የአኢተማ ልዩ ጽ/ቤት፣ የአኢተማ ቅርንጫፍ ማህበራት የሥራ አስከያጅ ኮሚቴ አባላት ስብሰባ ተካሂዶ ስለ ጠቅላላ ጉባኤው አካሄድ፣ ስለ አጀንዳ፣ ስለ ፀጥታ ከመን ጋገራቸውም በላይ ይህ የ18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ በትግል ጫዳ ለወደቀ ታጋይ ወዝ አደርቾ፣ አርስ አደርቾ፣ አብዮታዊ ምሁር፣ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ፣ በጉባኤው መጠረሽ የታሰሩት የህዝብ ወገኖች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፣ በመኢሶን አባልነትና ደጋፊነት በሚጠረጠሩ ላይ የሚደረገው ማሰደድ፣ ማሰር፣ ማፈንና መግደል በአስቸኳይ እንዲቆም፣ ዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ እንዲለቀቁ፣ ብሔራዊ ነፃነታችንና አብዮታችን የማይነጣጠሉ መሆናቸው የሚያሰይ፣ መኢሶን በኢት ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ትክክለኛ አቋም ያለው ሃቀኛ ተራማጅ ድርጅት መሆኑን የሚያረጋገጥ ስላማዊ ሰልፍ እንዲደረግ በአንድ ቃል ተስማሙ::

በኦገስት 1 ጠዋት የአኢተማ ሥራ አስከያጅ ሊቀመንበር ለጉባኤው የመክፈቻ ንግግር ከማድረጉ በፊት በአድሃሪያች ጥይት ተመተው ለወደቁ አንጋፋ ኮሚኒስቶች ለነደክተር ከበደ መንገሻ፣ ለነደክተር ተረፈ ወ/ጻድቅና እንዲሁም የሌሎች ታጋዮችንም ተጋድሎ አስከተቻለ ስም በመጥራት ለአንድ ደቂቃ እንዲያስታውሷቸው ጉባኤው ጠየቀ:: ከዚህ በኋላ መልእክት ይደረስ፣ ቀጥሎ መሪሪው ትግል የተሰኙት አብዮታዊ መዝሙሮች ተዘምሮ ጉባኤው ተከፈተ::

የማህበሩ ፕሬዚዳንት መጀመሪያ ስለዓለም አቀፍ የፖለቲካ ሁኔታ በ1/8/78 ጠዋት ሰፉ ያለ ንግግር አደረገ:: ከዚህ አለም አቀፍ የፖለቲካ ሁኔታ የመክፈቻ ንግግር መጠረሽ ''ዓለም አቀፍ'' የሚለው አብዮታዊ መዝሙር ተዘምሮ የ18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ተከፈተ::

የዓለም አቀፍ ንግግር እንዳለቀ ከአህት ማህበራትና ከልዩ ልዩ ድርጅቶች የአንድነት መግለጫ ተሰሙ:: የአንድነት መግለጫ የላኩና እንዲሁም በቴሌግራም ያስታወቁ የሚከተሉት ነበሩ::

1. የመላ ኢት ሶሻሊስት ንቅናቄ /መኢሶን/
2. የኢት ወጣቶች አብዮታዊ ንቅናቄ /ኢአወን/
3. በአውሮፖ የኢት ሴቶች ዲሞክራቲክ ማህበር /አኢሴዲማ/
4. በካናዳ ከሚገኙ ተራማጅ ኢትዮጵያውያኖች
5. በሎስ አንጀለስ የኢት ተማሪዎች የጥናት ክበብ



6. በግሪክ የኢትዮጵያውያን አንድነት ማህበር
7. በካይሮ የኢት ተማሪዎች ማህበር
8. በሱዳን የኢት ተማሪዎች ማህበር
9. በዩጋንዳ የኢት ተማሪዎች ማህበር
10. ጉባኤው እንዳይመጡ ከተከለከሉት በሶቪየት ህብረት ከሚገኙ አብዮታዊ ኢትዮጵያውን
11. SWEPO representative - Stockholm
12. Democratic Youth Legue of Finland
13. Partido Socialista - Chile
    Seccional Finlandia (representative in Finland)
14. The African Students Association in Finland (ASAF)
15. Antiimperialistischer
    Koordinations ausschuss (AKA) Heidelbert W. Germany
16. Lebanon Students organization from Czekoslavakia
    (svaz libanonskych studenta v. CSSR)
17. Zimbabwe Student Union in Prague
18. Frelimo's students in Czechoslovakia
    (Mozambique students in Czechoslovakia)
19. Union des estudiants Sènègalais
20. Comite de la juventud vanguardista en checoeslovaquia
21. Uganda Students Union in Czechoslovakia
22. Zimbabwe Students Union in Yougoslavia - Section - Belgrade
23. Association des etudiants
    Afgahan en Hongirie - Budapest
24. Organization of the Sudanees students in Bulgaria

በዚህ አለት በ1/9/78 ከሰዓት በኋላ 18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ሊቀ መንበር፣ ፀሐፊዎችና ኦዲተሮች ተመርጠው ሥራቸውን ቀጠሉ::

ከጉባኤው ሊቀመንበሩ ምርጫ በኋላ የአኢተማ ሥራ አስከያጅ ኮሚቴ የዓመቱ የሥራ ሪፖርር ቀረበ::

<u>የአኢተማ ሥራ አስከያጅ ሪፖርር</u>

በአውሮፖ የኢት ተማሪዎች ሥራ አስከያጅ የዓመቱ ሥራ ሪፖርር በሊቀመንበሩ ቀረበ:: የዓመቱ ሪፖርር በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነበር::

አንደኛው ክፍል የፖለቲካ ጥያቄን የያዘ ሲሆን የሥራ አስከያጅ ኮሚቴው ከ17ኛው ጠቅላላ ጉባኤ በኋላ ሥራውን ተረክቦ ባከናወነበት ወቅት ከኢት ዝበብጥ ሁኔታ ተነስቶ ያወጣቸውን የፖለቲካ መግለጫዎችና የወሰዳቸውን አቋሞች የሚያመለከት ነበር::

ሁለተኛው ክፍል የድርጅት ጥያቄ ሲሆን በዚህ ክፍል ውስጥ የሥራ አስከያጅ ኮሚቴው ከቅ/ማህበራት ፣ ከሌሎች እህት ማህበራት በተለይም ዓለም አቀፍ የኢት ተማሪዎች ማህበራትን ህብረት በሚመለከተው በኩል የአኢተማ ሃቀኛ ተማሪዎችን በዓለም አቀፍ ለማደራጀት ያደረገው ጥረትን የሚገልጽ ነበር::

ከዚህ ከሥራ አስከያጅ ሪፖርት በኋላ በሪፖሩ ላይ ውይይት ተከፍቶ ዓመቱን በሙሉ ሲሰራበት የነበረውንና ከዚም በፊት ማህበሩ የተከተለውን የፖለቲካ መስመር ለመረዳት ያቃታቸውና ለአለት ጥቅማቸው የአደሩ 7 ሰዎች የሥራ አስከያጅ ኮሚቴ ሪፖርት ተነበ አንዳለቀ ጉባኤውን ለቀው ወጡ:: በተረፈ በሪፖሩ ላይ ውይይቶ በጥሞና ተካሂዶ ዓመታዊ ሪፖሩ በሙሉ ድምፅ ድጋፍ ፀድቋል::

ከዛ የአኢተማ የመጽሔት ቦርዱና ልዩ/ጸ ቤት ሪፖርት ተነበበ::

የመጽሔት ቦርዱ ሪፖርም እንደዚሁ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍሎ፣ አንደኛው ስሩ ያለ የሀገሪቱ የፖለቲካ ትንተና ያዘለ ሲሆን፣ሁለተኛው ክፍል ስለመጽሔት ስለ ገንዘብ ችገርና የማስረጠትን ጥያቄ የሚያጠቃልል ነበር::

| በዚህ ዓመት የመጽሔት ቦርዱ:— | | ልዩ ጸ/ቤቱ |
|---|---|---|
| 1. ትገላችን ዜና | 6 | Ethiopian Review 3 |
| 2. ትገላችን | 2 | |
| 3. ታጠቅ | 1 | |
| 4. ነፃ ጋዜጦች | 5 | |

አውጥቶ መጽሔት ቦርዱ በአውሮፖ፣ በእስያ፣ በአፍሪካ፣ በአሜሪካ፣ በመካከለኛው ምሥራቅ፣ በአገር ቤት ..ወዘተ በብዛት አሰራጭቷል::

ከመጽሔት ቦርዱ ሪፖርር በኋላም ውይይት ተከፍቶ ሪፖሩን ቤቱ ሙሉ ለሙሉ ተቀብሎታል::



ከኮንግስት 2 ጠዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ የአኢተማ 15 ቅ/ማህበራት የሥራ አስከያጅ ኮሚቴዎች የዓመቱን ሥራቸውን የሚገልጽ ሪፖር አንዱ በአንዱ አቀረቡ:: በዚህ በቀረበው ሪፖር እያንዳንዱ ቅ ማህበር በዘረው በአገራችን አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ ፍፁም አብዮታዊ አቋም እንዳላቸው አንዱ ከአንዱ በኋላ በሚገባ ስለተነተኑ ጉባኤው ከመቸውም ጊዜ የበለጠ የአንድነት፣ የቆራጥነትና የጥራት መንፈስ ታይቶበታል::

ከዚህ በኋላ 2/8/78—4/8/78 ስድስት የስበሰበ ወቅቶች /ሴሽን/ የሚፈጁ ኮሚሽኖች በመከፋፈል ስለኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ በቀረቡት የመነደርደሪያ አርእስቶች ውይይት በየኮሚሽኑ ተጀመረ::

የ18ኛ ጠቅላላ ጉባኤ በቅርንጫፍ ማህበራት ሥራ አስከያጆች፣ በአኢተማ ሥራ አስከያጁና በመጽሔት ቦርዱ ፀድቆ የቀረበ የጥናት አርእስት፣

ክፍል 1

1. ድርጅትን በሚመለከት

ሀ- የወዝ አደሩ ፖርቲ ምንነትና አፈጣጠር
ለ- በወዝ አደሩ ፖርቲና በህዝባዊ ድርጅቶች መካከል ስላአለው ልዩነት
ሐ- ስለግንባር ምንነትና አመሠራረት

2. የትግል ሥልቶች

| | | |
|---|---|---|
| ህጋዊ የትግል ሥልት | ገልጽ የትግል ሥልት | የሰላም ትግል ሥልት |
| ህገወጥ " " | ህቡእ " " | አመጽ " " |

3. የዓለም ወዝ አደሮች ንቅናቄ ታሪክና አድርባዮች የዘወተት ሚና

ሀ - አድርባይነትና ታሪካዊ አመጣጡ
ለ - በዓለም ወዝ አደሮች ታሪክ ውስጥ አድርባዮች የዘወተት ሚና

ክፍል 2

1. የኢት ጊዜያዊ ሁኔታ በሚመለከተው

ሀ የአካባቢ ሁኔታ

የሰሜን አገር
የመሃል አገር

የምሥራቅና የደቡብ ምሥራቅ አገር

ለ- የኢኮኖሚ ጥያቄ በገጠርና በከተማ /የቀበሌና የገበሬ ማህበራት/

2. <u>ደርግና የኢት አብዮት</u>

ሀ_ የደርግ አረማመድና አቋቋም ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ፕሮግራም
አንፃር ሲታይ

ለ- የደርግ አረማመድ ከጥር ወዲህ

3. <u>ተጀምሮ ስለነበረው የኢማሊደህና የተነሱት ልዩነቶች</u>

| | |
|---|---|
| ሀ – በዲሞክራሲ | በዘመቻው /ህዝባዊ ሠራዊት/ |
| በቢሮክራሲ | በትጥቅ ጥያቄ |
| በብሔረሰቦች ጥያቄ | በአጠቃላይ በብሔራዊ ዲሞክራሲያ አብዮት ፕሮግራም |

ለ - የወጡትን መፈክሮች ሥራ ላይ በማዋልና በመተርጎም

ስለ አርዓታ
ስለ ራስን በራስ መርዳት
ብሔራዊ ነፃነት
አብዮታዊ እናት አገር ወይ ሞት
የነቃ፣ የተደራጀ፣ የታጠቀ የህዝብ አመጽ ወዘተ

<u>ክፍል 3</u>

<u>ተግባሮቻችን</u>

ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳን በሚመለከተው

4/8/78 በኋላ የውይይቶ ዋና ዋና ነጥቦች ከየኮሚሽኑ/ ከኮሚሽኖች ፀሐፊዎችና ሰብሳቢዎች ማቀነባበር በኋላ/ለጠቅላላው ጉባኤው አንድ በአንድ ቀርበው ከፍ ቶብቸው በሚገባ ተወይቶባቸዋል:: ከ 3 ቤሽን አንደገና ጠቅላላ ጉባኤ ውይይት በኋላ በውስኔ አዘጋጅ ኮሚቴዎች የ18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቀርቦ በውሳኔው ላይ ማሻሻያዎች ቢቀ በጠየቀው መሠረት ተደርጉባቸውና አንደገና ውስ ነው ሙሉ በሙሉ ተነበ በአንድ ተቃዋሚ በተቀረው ሙሉ በሙሉ ተደገፍ በጋለ ጭብጨባና አብዮታዊ ስሜት ፀድቋል:: ከዚያም ዓለም አቀፍን በመዘመር ውስኔው አለፈል::



ከዚህ በተረፈባሉት ቀናት ጉባኤ የኦዲተሮች ሪፖርት፣ የዶርጅት ችግሮችን አንድ በአንድ ተወያይቶ ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል:: በመጨረሻም ለመጭው ዓመት የሥራ አስከያጅና የመጽሔት ቦርድ ኮሚቴዎች በመምረጥ የአኢተማ ሥራ አስከያጅ የዱንዝሳሺያ ቀ/ማህበር ሲመረጥ፣ የመጽሔት ቦርዱን ሥራ የስዊድን ቅርንጫፍ ማህበር ተረከበል:: ከዚህ በተረፈ በመጨረሻው ቀን በበርሊን ከተማ ትልቅ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግና ከዚያም መልስ የመዝሙርና የግጥም ምሽት አድርጉ አብዮታዊ መዝሙሮችና ግጥሞች ለአባላት በሚያስደስት ሁኔታ ተዘጋጅተው ቀርበው ከተደመጡ በኋላ የ18ኛው ጠቅላላ ጉባኤ አካሄድ ስነ ሥርዓት ተፈጽሞአል::

## መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች

ሀ/ ወዝ አደሩ፣

የኢትዮጵያ አብዮት ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ የወዝ አደሩ መደብ ባደረገው ቆራጥ ትግል አያሌ ድሎችን ተጎናፅፏል:: ለምሳሌም፣ በመካከሉ ሰርጎ የገባውን እራሱን ኢህአፓ በማለት ይጠራ የነበረውን ግራ አድርባይ ደንፊ የንዑስ ከበርቴ ቡድን ከጉያው አውጥቶ በመጣል አብዮቱ እንዲራመድ አስተዋፅኦ አድርጓል:: እንዲሁም በሲአይኤ ተጽዕኖ ሥር የነበረውን የሰራተኛ ማህበር ኢሰአማ በመጣል በምትኩ አብዮታዊ የሰራተኞች መኢሰማ ማህበርን አቋቁሟል:: የመደቡንም ግንባር ቀደም ፓርቲ ለመፍጠርም ሆነ ሌሎች ህዝባዊ ድርጅቶችን ለማጠንከር ብሎም አብዮቱን እየመራ ከግቡ ለማድረስ በአሁኑ ጊዜ የዲሞክራሲ ጥያቄ በከፍተኛ ደረጃ የሚሰማው መደብ ነው::ለዚህም ዓላማ የቆሙ ታጋይ ወዝ አደሮች ዛሬ በመታሰር፣ በመገደል ላይ ይገኛሉ:: እንዲሁም በወዝ አደሩ በራሱ የተመረጡ መሪዎችእየተለቀሙ ስለሚታሰሩና ስለሚገደሉ በስንት ቆራጥ አብዮታዊ ትግል ያቋቋመው ማህበር በቀኝ አድርባዮችና በቢሮክራቶች ቁጥጥር ስር በመውደቅ ላይ ይገኛል:: ከዚህ አልፎ ተርፎ ደግሞ የሚያገኘው ደመወዝ በየጊዜው እየናረ ከሚሄደው የገበያ ዋጋ ጋር ስለማይመጣጠን የኑሮው ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመሄድ ላይ ይገኛል:: ለዚህ አስከፊ ሁኔታ መፈጠር ጊ.ወ.መንግሥት /ደርግ/ የተከተለው የፀረ አብዮትና የፀረ ዲሞክራሲያዊነት ጎዳና ከምክንያቶቹ አንዱ መሆኑን በደንብ እየተረዳው በመሄድ ላይ ይገኛል:: በተጨማሪም በቀኝ አድርባዮችና በጊ.ወ. መንግሥት የሚከናወነውን የኢህአፓን እንደገና ማንሰራራት ተፅእኖ በመቋቋምና "በቀኝ መንገደኞች" ስም ከመካከሉ እየተለቀሙ የሚታሰሩትንና የታሰሩትን ታጋይ ጓዶች እንዲፈቱ በመታገል ላይ ይገኛል::

ስለዚህ ሃቀኛ ተራማጆች ይህንን ሃቅ በመረዳት ወዝ አደሩን ከሚገኝበት አስከፊ ሁኔታ ራሱን ለማውጣት እንዲችል በጥንቃቄ መታገልና ማደራጀት ተግባራቸው ነው:: እንዲሁም በወዝ አደሩ ቀንበር ላይ የተቀመጡትንና ለመቀመጥ የሚፈልጉትን የወዝ አደር መስፍኖችን መታገልና መቃወም አብዮታዊ ግዴታቸው ነው::

ለ/ አርሶ አደሩ፣

እንደ ኢትዮጵያ ባለ ከፊል ጉልታዊና ከፊል ከበርቴ ህብረተሰብ ውስጥ የአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ዋና ተሸካሚ ኃይል ሰፊው አርሶ አደር ህዝብ ነው::



ከየካቲት 66 ዓ.ም. አብዮታዊ እንቅስቃሴ ወዲህ አርሶ አደሩ የማይናቁ ድሎችን ተጎናጽፏል:: መሬት ወደ አራሹ እጅ እንዲገባ የሚያደርግ አዋጅ ወጥቷል:: መጠናቸው የማይናቅ የገበሬ ማህበራት ተቋቁመዋል:: የገበሬ ማህበራት በአገር ዓቀፍ ደረጃ ተቋቁመዋል:: ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ከቢሮክራሲው፣ ከቀኝ አድርባዮችና ከደርግ በሚመጣው አሻጥር የተነሣ አርሶ አደሩ በመራራ ትግል ያገኘውን ድሎች ለማስጠበቅም ሆነ ለማስከበር ከማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል:: የዲሞክራሲ መብቶች ስለሌሉ ከዚህም ከዚያም የሚሸረቡበትን የፀረ ሕዝቦች አሻጥሮች ለማክሸፍና ብሎም የመደብ ትግሉን ለማፋፋም አልቻለም:: በአሁኑ ወቅት በብዛት የሚገመቱ ታጋይ አርሶ አደር መሪዎች ታስረዋል፣ ተገለዋል:: ከ1969 ዓ.ም. በጎጃም፣ በጎንደር፣ በሐረር፣ በከንባታና ሃዲያ በባሌ፣ በሲዳሞና በአርሲ አርሶ አደሮች ላይ የሰፈሩና የሚሊታሪው ቢሮክራሲ ከፍተኛ ጭፍጨፋ አድርሶባቸዋል:: በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ የመደብ ትግሉ በመቀዛቀዙ ምክንያት የብሔረሰቦች ጥያቄ እየተስፋፋ በመምጣት ላይ ይገኛል:: የደቡብ ብሔረሰቦች በብሔረሰብ ጥያቄ አካባቢ ለመደራጀት መጀመር ለዚሁ ምስክር ነው:: በወሎ፣ በትግራይና በሰሜን ሸዋ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ደሃ ገበሬ በርሃብ አለንጋ በመገረፍ ላይ ይገኛል:: ስለረሃቡ ጉዳይ ከዛሬ አራት አመት በፊት ለደርጉ የተጠና ጥናት ቀርቦለት እንደነበር የሚታወቅ ነው:: ስለዚሁ ረሃብ ጉዳይ ደርግ ዛሬ ቢናገርም እንኳን ለደሃው ገበሬ ዕልቂት በኃላፊነት ተጠያቂ ነው::

ከዚህም በላይ የሸቀጣሸቀጦች ማጠርና ከዚያውም ያሉትም ዋጋቸው መናር አርሶ አደሩን አስከፍቶታል:: አርሶ አደሩ ከደረሰበት ችግሮች ለመውጣትና ከየአቅጣጫው የሚመጡትን ፀረ ሕዝብ አሻጥሮች ለማክሸፍ እንዲያስችለው የዲሞክራሲ መብት መኖር ወሳኝ ነገር ነው::

ምንም እንኳን በአሁን ሰዓት በሃቀኛ ተራማጆች ላይ የሚደረገው ፀረ ዲሞክራቲክ እርምጃ እስራት፣ ክትትልና ግድያ ከፍተኛ ቢሆንም ቀሉ በገጠር ውስጥ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ለተራማጆች በገጠር ተሰማርተው ለመሥራት አመቺ በመሆኑ ጥንቃቄ በተመላበት መንገድ ተሠማርተው እንዲሰሩ የአኢተማ 18ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ያቀርባል::

መኢሶንና ኢጭአት ከገበሬው ጋር ያላቸውን ጥሩ ግንኙነት ለማራከስ "ጠባብ ብሔርተኛ" "ቀኝ መንገደኛ" ገበሬዎች እየተባሉ በአርሶ አደሩ ሕዝብ ላይ የሚደረገውን አድሃሪ ቅስቀሳ ማህበራችን ያወግዛል::

ሐ/ ገዐስ ከበርቴው፤

እንደ ኢትዮጵያ ባለች ወደ ኋላ በቀረች አገር የዚህ መደብ አባሎች ቁጥር በጣም ብዙ ነው:: ይህም መደብ እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ የአብዮቱ አጋዥና ወገን ይሆናል:: የዲሞክራሲ መኖርም የሚፈልግና የዲሞክራሲ መጥፋትም በጣም የሚያስቀጣው ከመሆኑ አልፎ ለዚህ መብት መኖር እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ የሚታገል መደብ ነው:: የኢትዮጵያን ዝሀያዊ ሁኔታ ለተመለከተ በአሁኑ ሰዓት የጊ.ወ.አ.ደርግ የሚወስዳቸው ፀረ ዲሞክራቲክ እርምጃዎችና የተሣሣተ የፖለቲካ መስመር ከፍተኛ አስቆጥቶታል፤ በአሁኑም ሰዓት በሃገሪቷ ላይ የወደቀው የኑሮ ውድነትና የእቃ ዋጋዎች መናር ይህንን መደብ ከፍተኛ አስቆጥቶታል:: ስለሆነም በአሁኑ ሰዓት ይህንን መደብ ክፍል በጥንቃቄ መያዝና በበለጠ ወደ ፀረ አብዮት ወገን እንዳያዘነብል መታገል ያስፈልጋል:: ስለዚህ ከዚህ መደብ ክፍሎች ውስጥ የብ.ዲ.አብዮት ፕሮግራምን ተቀብለው ወደ አብዮቱ ሰፈር ሊሰለፉ የሚችሉትን ኃይሎችን አብዮት ውስጥ እንዲሰለፉ ማድረግና ከገዐስ ከበርቴው ደገፊ በድን /ኢህአፓ/ የከሰረ የፖለቲካ መስመር ብዙ ትምህርት እንዲቀስሙ ማድረግ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው:: ለዚህም ማህበራችን ከዚህ መደብ ክፍሎች ለአብዮት ሊሰለፉ የሚችሉትን ኃይሎች ወደ ፀረ አብዮት ሰፈር ሰምጠው እንዳይገቡ ጥንቃቄ በተሞላበት የቅራኔዎች አያያዝ በአብዮቱ ሠፈር እንዲሰለፉ ለሚደረገው ትግል በአብዮታውያን ጎን ሆኖ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል::

መ/ ብሔራዊ ከበርቴው፤

እንደኢትዮጵያ ባለች ከፊል ፊዩዳልና ከፊል ከበርቴ አገር ብሔራዊ ከበርቴው በመሠረቱ ደካማና ወላዋይ ነው:: ሆኖም ይህ መደብ ከፊዩዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ባለው ቅራኔ የተነሳ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ እስከተወሰነ ደረጃና እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ሊሳተፍ ይችላል:: በተለይም እዚህ መደብ ውስጥ የተወሰነ ክፍሉ አገር ወዳድ ስለሆነ በአብዮቱ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይችላል:: ይህ መደብ በብሔራዊ ዲሞክራሲ አብዮት ወቅት ይቀርና በህዝባዊ መንግሥት ዘመንም ተፈላጊነት ያለው የካፒታልና የሰው ጉልበት ዛሬም ሆነ ነገ ለኢኮኖሚ እድገት ጠቃሚ ስለሆነ ብሔራዊ ከበርቴው በጥንቃቄ መያዝ አለበት::



በአሁኑ ሰዓት በአገራችን ውስጥ ብሔራዊ ከበርቴው በጥንቃቄ ባለመያዙና የጊ.ወ.ደርግም ፀረ ዲሞክራሲያዊ የሆነ የጉልበት ፖሊሲ በመከተሉ በብሔራዊ ከበርቴው ላይ ጥፋት እርምጃ እየተወሰደበት ነው:: አገሪቱ ለደረሰባት የኢኮኖሚ ውድቀት ሁሉ መንግሥት ብሔራዊ ከበርቴውን ተጠያቂ እያደረገ እራሱን ከኃላፊነት ለማሸሽ በመሞከር ላይ ነው:: በአንፃሩም አስፈላጊ ርምጃ ባለመወሰዱ ብዙ ካፒታል ባክኖ ይገኛል:: ስለሆነም ደርግ በሚከተለው የተሳሳተ ፖለቲካ ምክንያት ብሔራዊ ከበርቴው በሚገባ በኢኮኖሚ ዘርፍ እንዳይሳተፍ አግዶታል:: ይህ አደገኛ አዝማሚያና ጥፋት ፖሊሲ ብሔራዊ ከበርቴው ወደ ፀረ አብዮት ሰፈር እንዲጓዝ ገፋፍቶታል::

ስለሆነም ማህበራችን ሀቀኛ ተራማጆች የዚህን መደብ አያያዝ በደንብ እያጤኑ ለብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ሊሰለፉ የሚችሉ ብሔራዊ ከበርቴዎችን በትክክለኛ አብዮታዊ መስመር እንዲያዙ ደርጉ በዚህ መደብ ላይ የሚከተለውን ጥፋት ፖሊሲ እንዲያወግዙ አብዮታዊ ጥሪ እያቀረበ አገሪቱ ከገባችበት የኢኮኖሚ ክሪዝ እንድትወጣ ለሚደረገው ትግል ብሔራዊ ከበርቴው ተገቢ ተሳትፎውን እንዲያሳይ ለሀቀኛ አብዮታውያን የትግል አንድነትን ይገልጻል::

ሠ/ መለዮ ለባሹ፤

መለዮ ለባሹ በመደብ ምንጩ ከሰፊው ህዝብ ወገን በመሆኑና የፊውደ ፋሽስቱ ስርዓት ከሚጨቁናቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አንዱ በመሆኑ በየካቲት 66ዓ.ም. የህዝብ እንቅስቃሴ ውስጥ ከጭቁኑ ሕዝብ ጎን በመቆም ለዲሞክራሲና ለእኩልነት ከፍ ያለ ትግል አካሂዷል:: አሁንም ለዚሁ አላማ እየታገለ ነው:: ጊ.ወ.አ.ደርግ መለዮ ለባሹን በፀረ ዲሞክራሲያዊ አገዛዙ ቁጥጥር ስር ለማድረግና ለዲሞክራሲ መብታቸው የሚታገሉትን ሃይሎች መደምሰሻ መሳሪያ ለማድረግ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጣር ላይ ይገኛል:: ሆኖም በመለዮ ለባሹም ውስጥ የደርግን አጉል ጥረት በመቃወም አሁንም ለዲሞክራሲና ለእኩልነት የሚደረገውን ትግል ለማፋፋም የሚጣጣሩ ብዙ ታጋይ ሀይሎች ይገኙበታል::

መለዮ ለባሹ ለብሔራዊ ዲ.አብዮት ፕሮግራም የገባውን ቃልኪዳን ለማክበር ሲታገል ከመካከሉ ከወጡ በ" ካድሬ" ስም አደርባዮች እየተመለመሉ ስለተጫኑበት በአንድ በኩል ከሚሊቴሪ ቢሮክራሲው ጋር ፣ በሌላ በኩል ከአዲሶቹ ምልምል አደርባዮች ጋር ቅራኔ ውስጥ ወድቋል:: ከዚህም ሌላ አድሃሪው ዚያድ ባሬ በምስራቅና በደቡብ

ምስራቅ በከፈተብን ጦርነት ወቅት በደርግ ፀረ ዲሞክራሲነትና በቢሮክራሲው አሻጥር ምክንያት በሃገራችን ላይ በደረሰው ጉዳት እጅግ የተቀጣ የህብረተሰብ ክፍል ነው:: ብዙ ግንባር ቀደም የሆኑ መለዮ ለባሾች የደርግ ፀረ ዲሞክራሲ አገዛዝ መሳሪያ መሆናቸውን ተረድተው "ከህዝብ ተጣላን"፣ "ተቀያየምን" "ተራራቅን" በማለት ከፍተኛ እሮሮዋቸውን እያሰሙ ናቸው:: ሃቀኛ ታጋይ መለዮ ለባሾችም በእስራትና በመሰደድ ላይ ይገኛሉ:: ስለሆነም በነዚህ ሃቀኞች ላይ የሚካሄደው ፀረ ዲሞክራሲ እርምጃ ባስቸኳይ እንዲቆም በአብዮታዊና አገር ወዳድ መለዮለባሾችና የጦር መኮንኖች ላይ የሚደረገው ክትትል እንዲወገድ የአኢተማ 185ኛ ጠ/ጉባዔ ይጠይቃል:: ጭቁን መለዮ ለባሾች ከሰፊው ህዝብ ጋር ሆነው ለዲሞክራሲና ለእኩልነት የሚያደርጉትን ትግል ጉባኤው ይደግፋል:: ታጋይ መለዮ ለባሾችም ከሃቀኛ ተራማጆችና ከሰፊው ህዝብ ጎን እንዲቆሙና መለዮ ለባሾች እንደ ኃይለ ሥላሴ ዘመን አሁንም የሕዝብ ማፈኛና መጨቆኛ መሳሪያ እንዳይሆኑ ነቅተው መጠበቅና ቃልኪዳናቸው ለብ. ዲ. አ. ፕሮግራም እንጂ ከሱ ለሚንሸራተተው ኃይል እንዳልሆነ እንዲረዱ ጉባኤው አጥብቆ ይጠይቃል::

ረ/ <u>አገር ወዳዶችና ዲሞክራቶች፣</u>

እነዚህ ሃይሎች በብሔራዊ ዲሞክራሲ አብዮት ውስጥ ትልቅ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ ሆነው ይገኛሉ:: ብዙን ጊዜም በንዑስ ከበርቴው መደብና በብሔራዊ ከበርቴው መደብ ውስጥ በቡድን ወይንም በግለሰብ ደረጃ ሊገኙ ይችላሉ:: ይህም ሃይል ከኢትዮጵያ አገባር በተለይ በሃገራችን ብሔራዊ ነፃነት በኢምፔሪያሊስትና በአድሃሪ ኃይሎች መደፈር ምክንያት በጣም የሚቆጩና የሚቀረቀሩ ከመሆናቸውም በላይ ትልቅ ተጋድሎ የሚያደርጉ ናቸው:: ምንም እንኳን በሃገራችን ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለው ጭፍን ፀረ ሕዝብ ጭቁና ፀረ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ትልቅ እንቅፋት ቢሆንባቸውም ቀሉ በአሁኑ ሠዓት ለሃገራቸው ብሔራዊ ነፃነትና ለዲሞክራሲ ከሚያደርጉት ትግል ሊያግዳቸው አልቻለም:: እነዚህ ሃይሎች በአሁኑ ሠዓት የጊ.ወ.መንግሥትና አድርባይ ድርጅቶች የተከተሉት ፀረ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ዘለቄታ የሌለውና ዘር ዘር ውድቀትን እንደሚያስከትል እየተረዱት ነው:: ሰፊው ሕዝብ ጎንም በመሰለፍ ለብሔራዊ ነፃነትና ለዲሞክራሲ በሚደረገው ትግል ውስጥ አብዮታዊ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ:: ይህንንም በመገንዘብ ከአብዮቱ ወገን ትልቅ እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል:: በመሆኑም ሃቀኛ ተራማጆችና አገር ወዳድ ዲሞክራቶች ከአሁኑ አንድ የጋራ ትግል ግንባር ፈጥረው ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ተቀብለው ለብሔራዊ ነፃነትና ለዲሞክራሲ የሚያደርጉትን ትግል በበለጠ ያካሄዱ ዘንድ ይህ ጉባዔ አብዮታዊ ጥሪውን ያደርጋል::

ሰ/ ስለ ወጣቶች
ሸ/ ስለ ሴቶች /ቁ.5. ሐ — መ ተመልከት/



2. <u>ስለ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት፣</u>

ማህበራችን በጊ.ወ.ደርግ ላይ ያለው አቋም አብዮታዊ ሆነ ነው:: ጊ.ወ. መንግሥት የንዑስ ከበርቴ መንግሥት ነው:: የአብዮታዊነትም የአድሃሪነትም ጠባይ እንዳለው፣ በዚህ ተለዋዋጭ ጠባዩ አንድ ጊዜ በአብዮቱ ሰፈር እየቆመ በሌላ ጊዜ ደግሞ አብዮቱን እያጠቃ እንደሚራመድ ማህበራችን በተደጋጋሚ አስምቷል:: ሰፊው ጭቁን ሕዝብ የሱ ተከታይ እስከሆነ ድረስ የተራማጅነት ጠባይ ሲያመዝን፣ ሰፊው ሕዝብ ነቅቶ፣ ተደራጅቶና ታጥቆ ቀደምት ሊሄድ ሲል ደግሞ እድገቱን ለመቀጨት በሚፈጽማቸው ድርጊቶች አድሃሪ ገጽታውን ያሳያል::

ይሁን እንጂ ከአንድ ዓመት ወዲህ እየተጫወተ ባለው ሚና፣ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በስንት ትግልና መስዋትነት ያገኘውን፣ የደገፈውንና ያቀፈውን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እየከዳ በመምጣቱ አብዮቱን ለማጥቃት ያለው ጠባይ እያየለ መምጣቱና እስከ ደረጃላይ መድረሱ ለማንም ሐቀኛ ገለጽ ነው::

በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት ሐቀኛ ተራማጆችን ለመርዳት፣ ህዝባዊ ድርጅቶች እንዲያብቡ እንዲነቁና እንዲታጠቁ የሰፊው ጭቁን ህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ በአስቸኳይ እንዲታወቁ የገባቸውን ቃል ኪዳኖች በመካዱ፣ ከለየላቸው የቀኝ አድርባዮችና ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር ሕብረት ፈጥሮ ሐቀኛ ተራማጆችን እየረሸነና በእሥርቤት እያጎረ በማሰቃየቱ፣ ሕዝባዊ ድርጅቶችን በማንአህሎኝነት እያፈራረሰ በመሆኑ፣ በብሔር ትምክህተኝነት ተወጥሮ በመያዙ፣ ከሰፊው ሕዝብና ከአብዮታውያን ጋር ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ እየገባ ሄዷል::

ከዚህም ሌላ እጅግ በጣም አሳሳቢ የሆነውን የአብዮታችንንና የብሄራዊ ነፃነታችንን ጥያቄ በሰፊው ሕዝብ ላይ በመተማመን መፍትሄ ከማግኘት ይልቅ በአድሃሪው ቢሮክራሲና በውጭ ሃይሎች ጫንቃ ላይ እንዲወድቅ አድርጋል:: በአሁኑ ሰዓት በአብዮታችን ላይ ሆነ በብሔራዊ ክብራችንና ነፃነታችን ላይ የሰፈረት አደጋዎች ሁሉ የሚመነጩት ጊ.ወ.መንግሥት ከአድርባይ ድርጅቶችና ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር ህብረት ፈጥሮ ከብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አንፃር ከሚያሳየው ክህደትና መንሸራተት እንደሆነ ገለጽ ነው::

በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ጊ.ወ.መንግሥት ከሚያደርገው ክህደትና መንሸራተት የተነሳ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መድረክ ላይ ከቆሙ ሃይሎች ጋር ያለው ቅራኔ ወደ እንደኛ ደረጃ የሚለወጥበት ወቅት ሩቅ አይሆንም:: በዚህ

የክህደት ጉዳና እስከ ቀጠለ.ድረስ አብዮታችንና ሃገራችንን ወጥረው ከያዙት ችግሮች አንዱንም መፍታት እንደማይቻል እንዲያውም ችግሮቹ እየተባባሱ ሄደው የለየለት ቀለበስ ሊከተል እንደሚችል ማህበራችን ያስታውቃል::

በዚህ አንፃር ጊ. ወታደራዊ መንግሥት በማሳየት ላይ ያለውን ክህደት ማህበራችን በጥብቅ እያወገዘ በኢትዮጵያ አብዮት በብሄራዊ ክብራችንና ነፃነታችን ላይ ለሚደርሰው ማናቸውም ጥቃት ከለየላቸው አድሃሪያችና አገልጋዮች ጋር በታሪክ ፊት ደርግ ተጠያቂ እንደሚሆን ያስገነዝባል::

እንዲሁም ጊ.ወታደራዊ መንግሥት በአብዮታዊያን፣ በሰፊ ተራማጆች ወዝአደሮች አርሶ አደሮች አብዮታውያን መለዮ ለባሾች ታጋይ ወጣቶች፣ ታጋይ ሴቶች፣ ጭቁን የብሔረሰቦች ታጋዮች...ወዘተ፣ እንዲሁም በመኢሶን አባላት፣ ደጋፊዎችና ወዳጆች ላይ በተለይ የሚያደርገውን ግድያ፣ ማሳደድ፣ አፈና እሥራት... ማህበራችን በጥብቅ እያወገዘ ይህ ፀረ አብዮት ድርጊት አሁኑኑ እንዲቆምና በእሥር ላይ የሚገኙት ባስቸኳይ እንዲፈቱ 18ኛው በአ/ኢ/ተ/ማ ጉባዔ አጥብቆ ይጠይቃል ::

ለብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ታማኝ የሆኑ ፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ሃይሎች ማለትም ወዝ አደሮች፣ አርሶ አደሮች መለዮ ለባሾች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አብዮታዊና አገር ወዳድ መምህራንና የጠርና የፖሊስ መኮንኖች፣ ብሄራዊ ከበርቴዎች፣ የጭቁን ብሔረሰቦች ታጋዮች፣ ሌሎች ዲሞክራቶችና አገር ወዳጆች ሁሉ በደርጉ ውስጥም ያሉት ጭምር ይህንን የጊ.ወ.መንግሥት ክህደት እንዲያጋልጡና እንዲያወግዙ ይህ ጉባዔ ጥሪ ያደርጋል::

እንዲሁም የብ/ዲ/አብዮት ፕሮግራም በሚሰጣቸው መብት ተጠቅመው እነዚህ ሃይሎች ሁሉ በየደረጃቸውና በየፈርጃቸው ለመደራጀት የሚያደርጉትን ጥረት እንዲያፋፍሙ በአ/ኢ/ተ/ማ 18ኛ ጠ/ዓመታዊ ጉባዔ ጥሪ ያደርጋል::



3. ስለብሔራዊ ነፃነታችን ጉዳይና ስለ ራስን በራስ መቻል፣

በዚህ ጉዳይ በአ.ኢ.ተ.ማ. ሆነ፣ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ፣ ሌሎች ሃቀኛ ተራማጆች በተደጋጋሚ "ዕርዳታ ድጋፍ እንጂ ወሳኝ አይደለም" "ወደ ወሳኝነት የተላለፈ ዕርዳታ ለአብዮታችንም፣ ለሃገራችንም ብሄራዊ ነፃነት አደገኛ ነው" በሚለው አብዮታዊ መርህ ስር ተሰልፈው ከፍ ያለ ቅስቀሳ እንዳካሄዱ ይታወሳል::

"ዓለም ዓቀፋዊ" ተብሎ ስለሚመጣው ዕርዳታ በማርክሲስቶችና በገዐስ ከበርቴው መሀል ልዩነቶች እንዳሉ ግልጽ ነው:: "የውጭ ዕርዳታ" "ስለ ራስን በራስ መቻል" ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ያለባቸው ከመደብ ትግል አንፃር በመመልከት ነው::

አብዮታውያን ራስን በራስ መቻል በሚለው መርህ ቅድሚያ ይሰጣሉ:: ይህንን ማድረጋቸው ግን የውጭ ዕርዳታን መቃወማቸው ወይም ዓለም ዓቀፋዊነትን መሰረዛቸው አይደለም:: ሃቀኛ ዓለም አቀፋዊነት <u>አብዮትን ለማራመድ</u> የሚረዳ ዓለም ዓቀፋዊነት ብቻ ነው:: በዓለም አቀፋዊነት ስም የሚመጣ ዕርዳታ አብዮትን ሊያራምድ የሚችለው በአጋዥነት ደረጃ ሲሰለፍ ብቻ ነው:: የውጭ ዕርዳታን በወሳኝ ደረጃ ማሰለፍ ከቁከረ አብዮትን ያደናቅፋል:: ዓለም ዓቀፋዊነትን ይፃረራል::

ቀለባሽ ኃይሎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ የውጭ ዕርዳታ እንዳይደርስ ይፈልጋሉ እነሱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕርዳታ እያስተባበሩና እያገኙ አብዮቱ ግን የነሱን ፀረ ህዝብ ሕብረት ብቻውን እንዲጋፈጥ ይሞክራሉ::

በውስጥ ያለው የአብዮቱ ሰፈር በታሪክ ፈጣሪው በኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዕምነት አለው፣ አብዮትን ከግቡ ሊያደርስ የሚችለው ወሳኝ ኃይል የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ብቻ መሆኑን ያምናል፣ወሳኝ ጉልበቱን ሕዝቡን ለማንቃት ለማደራጀት ለማስታጠቅ ባጥሩ አገሪቱን የአብዮት ምሽግ ለማድረግ ያውላል፣ በዚህ መንፈስ የዚህ አብዮት ዓለም ዓቀፍ ወዳጆቹ በፓለቲካ በኢኮኖሚ በማቴሪያልና በሚሊቴሪ የመርዳት ኃላፊነት ስላለባቸው ለጋራው ትግል ዕርዳታ ይሰጣሉ:: ነገር ግን ይህ ዕርዳታ በምንም ዓይነት የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀውን ትግል ሂደት የሚተካ በሰፊው ህዝብ ቦታ አብዮቱን ከግቡ አደርሳለሁ የሚል ዕርዳታ መሆን አይችልም::

ባንፃሩ <u>የውጭ ዕርዳታን በወሳኝነት ደረጃ</u> ማስቀመጥ የሚገደዱ በህዝቡ ሊተማመኑ የማይችሉና የማይሹ ውለው አድረው በፀረ ህዝብ ዓላማቸው የሚጋለጡ ኃይሎች ናቸው::

በአገራችን የውጭ ዕርዳታ ጉዳይ በማርክሲስቶችና በነውስ ከበርቴው መካከል በተዘባጭ ሁኔታ አከራካሪ እየሆነ የመጣው እንዳለማየሁ ኃይሌ ተደምስሰው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም <u>በውስጥ ተላከቂ</u> በተለይ በውጭ ኃይሎች እየተጠቀመ አብዮታችንን ማጥቃት ከጀመረ ካንድ ዓመት ወዲህ ነው::

ደርግ በሰፊው ህዝብ ላይ ሳይሆን <u>በቢሮክራሲው ላይ መተማመን</u> እንደመረጠ ሁሉ የውጭ ዕርዳታንም እንደዚሁ የህዝቡን ትግል <u>መተኪያና</u> ቀስ በቀስም አብዮቱን ፈር ማስያዣ አድርጎ ተጠቅሞበታል:: ህብረት መፍጠር የጀመሩት ደርግና ቢሮክራሲ በውጭ ዕርዳታ ተማምነው የነቃ፣ የተደራጀ የታጠቀ የህዝብ ትግልን ለመተካት እየተፍጨረጨሩና ከውጭው ዕርዳታ መጨመር ጋር ነውስ ከበርቴው የህዝቡን ትግል ለመተካትና የራሱን ስልጣን ለማደላደል ሞክሯል:: የተፈጠረው የደርግና የቢሮክራሲው ህብረት በዕርዳታው የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ህዝብ ትግልን ለማራመድ ሳይሆን እሱን ለመተካት እንደተጠቀመበት አብዮታችን ከውስጥ ተበርቡሮ ዛሬ የሚገኝበት አደገኛ ሁኔታ መድረሱ ምስክር ነው::

በአሁኑ ወቅት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የመኢሶን አባላት በእስር ላይ መገኘታቸው እንዲሁም የቀበሌ፣ የገበሬ፣ የወዝ አደር መሪዎች፣ ተራማጅ መለዮ ለባሾች፣ አብዮታዊያን አገር ወዳድ የአየር ኃይል፣ የምድር ጦር መኮንኖች በእስር ላይ መገኘታቸውና የተራማጆችን ህብረት እንዳለነበረ አድርጎ የሚያወድም ፀረ ዲሞክራሲ መንገስ የቀኝ ኃይሎች ህብረት የውጭ ዕርዳታን <u>ለነቃ፣ ለተደራጀና ለታጠቀ ህዝብ ዐመፅ መተኪያ ብቻ ሳይሆን ይህንን አብዮታዊ ፈር ለማስለቀቂያ እንደተጠቀሙበት የሚያሳይ ነው::</u>

ባሁኑ ወቅት የህዝቡን ትግል በመፍራት በአድሃሪው ቢሮክራሲና በውጭ አርዳታ መተማመንን የመረጠው ደርግ በዚህ ዕርዳታ እየተጠናከረና ፀረ ህዝብ ገጽታውን እያጎላ በመሄድ ላይ መሆኑ ከአንድ ዓመት ወዲህ በኢትዮጵያ ፀረ አብዮት እንጂ አብዮት እየተጠናከረ አለመምጣቱ ገለጸ ነው::

በዓለም ዓቀፋዊነት ተነሳስተን የኢትዮጵያን አብዮት እንረዳለን የሚሉ ኃይሎች ይህንን ሁኔታ እንዲያጤኑና የደርግን ፀረ ህዝብ ገፅታ በማጠናከር ከቀለበሰው ታሪካዊ ኃላፊነት እንዳይጋሩ ማህበራችን ያስጠነቅቃል::



## 4. <u>አድርባይ ድርጅቶች፣</u>

አድርባይ ድርጅቶች / ሰደድ፣ወዝና ማሌሪድ/ በአሁኑ ወቅት "ሶስት ድርጅቶች" ተብለው የሚጠሩበት ወቅት አከትሟል:: በፖለቲካ አቋማቸው ሙሉ በሙሉ አንድ ናቸው:: ከብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም፣ከመርሃ ግብሩና ከራሳቸው ፕሮግራም ተገሸራቀው የሚከተሉት ፀረ አብዮት ፖለቲካ አንድነው::

የወዝና የማሌሪድ አመራሮች የድርጅታቸውን ህልውና ለፍርፋሪ ሸጠው በአሁኑ ጊዜ አሉ ለማለት የማይችሉ ከሰደድ ስር ጠቅልለው የገቡ አገባዳድ ድርጅቶች ናቸው::

<u>አብዮታዊ ሰደድ፣</u>

ይህ ድርጅት በአሁኑ ወቅት ስልጣን የጨበጠ ድርጅት ነው:: ከሃቀኛ ተራማጆች አንስቶ እስከ አድሃሪና ፀረ ኮሚኒስት የሲቪልና የሚሊቴሪ ቢሮክራቶች በአባልነት የሚጋፋበት ድርጅት ነው:: በውስጡ መጠነኛ ትግል ቢካሄድም ሃቀኛ መለዮ ለባሾችና አብዮታዊ መኮንኖች ድምፃቸውን የሚያሰሙበት ሁኔታ አላገኙም:: በአሁኑ ወቅት አመራሩ የሚከተለው ፀረ ዲሞክራሲያዊ፣ ፀረ ብ.ዲ.አ.ፕሮግራም፣ ትምክህተኛ ከሰፊው ሕዝብ ጋር ሳይሆን ከቀኝ ኃይሎች ጋር የተጠናከረ የህብረት ፖለቲካ፣ በሰፊው ሕዝብ ሳይሆን በውጭ ኃይሎች ላይ የመመካት አዝማሚያ፣ በአብዮታዊያን ላይ የሚያካሄደው ዘመቻ...ወዘተ አድርባይና አብዮቱን ለቀለበሳ የሚያመቻቹ የሃገራችንን ከበርቴ እንዳለነበረ አድርጎ የሚያጠፉ ፖለቲካ ነው:: አብዮታዊ ሰደድ በአሁኑ ወቅት ደርግንም ሆነ ኢማሌዲህ ውስጥ አሉ የሚባሉትን ሌሎች ድርጅቶች ከሙሉ ቁጥጥር ስር አውሏቸዋል::ቢሆንም በደርግ ውስጥ አንዳንድ የማይፈለጉ አባላትን በማባረርና በሰደድ ውስጥ የሚገኙ ቀንደኛ አባሎችን ወደ ስልጣን ለማውጣት እንደዚሁም ነውስ ከበርቴው መደብ ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር የጀመረውን ህብረት አጠናክሮ ድርጅታዊ መልክ ለመስጠት "የወዝ አደር ፓርቲ" ለማወጅ ሽርጉድ በማለት ላይ ነው:: በአዋጅ ይፈጠራል የሚባለው "የወዝ አደር ፓርቲ" በዚህ ሁኔታ የአብዮታዊ ሰደድ ሌላ መጠሪያ ስም እንደሆነ ገለጸ ነው::

<u>የወዝ አደር ሊግ፣</u>

በአሁኑ ሰዓት ይህ ድርጅት ምንም ዓይነት የራሱ የሆነ ህልውና የለውም:: የደርግና የአድሃሪው ቢሮክራሲ ህብረት ተቀጥላ የሆነ ድርጅት ነው:: በፖለቲካም ሆነ በድርጅታዊ አቋሙ ከአብዮታዊ ሰደድ አይለይም:: አመራሩ በከፍተኛ አድርባይነት የተጥለቀለቀ በመሆኑ ምንጊዜም መለያ ምልክቱ በአንገብጋቢ የአብዮትና የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ አድፍጦ መኖሩ ነው:: በአንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ ሁሉ ለአብዮታዊ ሰደድ ያጋደደ ፀረ አብዮት አቋሞችን በአብዮታዊ ቲዎሪ ሽፋፍኖ ለማሳለፍ የሚሞክር "ድርጅት" ነው::

በዚህ ጥረቱ ግን ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም ጋር ጠርሰ የማይተዋወቅ ድርጅት መሆኑን ከማጋለጡ በላይ የራሱ የሆነ ሀሳብና ስለሌለው ዛሬ የወዝ አደር ሊግ የተባለ ማ.ሌ. ድርጅት አለ ለማለት ያስቸግራል::

ማሌሪድ "ማርክሳዊ" "ሌኒናዊ" ረቮልሽናዊ" ድርጅት"

ኢህአፓ መከሰርና መጋለጥ ስትጀምር ፈለሰው "ወደ አብዮት" ሰፈር ተደባልቀናል ያሉ አድርባዮች የመሰረቱት "ድርጅት" ነው።እንደተቋቋመ ከፕሮግራሙ ያወጣቸው ከነበረት ጽሁፎች በመነሳት ሃቀኛ አብዮታዊያን ድጋፋቸውን ሰጥተውት ነበር:: ከዚያም አልፎ ከመኢሶን ጋር ህብረት መስርቶ ነበር:: ነገር ግን እንደሌሎቹ አድርባይ ድርጅቶች መገሸራቱት ሲጀምር ከመኢሶን ጋር የነበረውን ህብረት አፍርሶ ለአብዮታዊ ሰደድ አገብድቷል:: በዚህም አቋሙን በሙሉ ከደና ለደርግና ለአብዮታዊ ሰደድ አገብድዶ ዛሬ እስከሀልወናው ያጣ "ድርጅት" ነው።ፀረ አብዮት እያየለ ከመጣበት ከሚያዝያ ወር 1969 ዓ.ም. ወዲህ አቋሙን በ180 ዲግሪ ቀይሯል::ከመኢሶን ጋር በነበረው ግንኙነቶች የሚያውቃቸውን ምስጢሮች ለጠላት አሳልፎ በመስጠት የመኢሶንን የሀቡዕ አባላት ደጋፊያችና ወዳጆች በመጠቆም ለእስራት ለእልፈትና ለግድያ አያሳለፈ ሰጥቷል:: ከኢህአፓ ጋር ቀደም ሲል በነበረው ግንኙነት በመጠቀም "የቀደሞ" የኢህአፓ አባላት ለሚባሉ ፀረ አብዮተኞች በረን በሰፊው በመከፈት ለኢህአፓ ትንሣዔ ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኗል::

እነዚህ ሶስት ድርጅቶች /ሰደድ ፣ ወዝ ሊግና ማሌሪድ/ የተቀበሉትን የብ.ዴ. አብዮት ፕሮግራምን እየከዱ በፀረ አብዮት ጎዳና በመሰለፋቸው በአብዮት ላይና በተራማጆች ላይ ይህ ነው የማይባል ጥቃት በማድረሳቸው የኢትዮጵያን ብሔራዊ ነፃነትና ሕልውና ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር በማበር በማስደፈራቸው ማህበራችን እነዚህ ሶስት ድርጅቶችን ባባዮት ክህደትና መገሸራቱት በጥብቅ ያወግዛቸዋል:: የሚከተሉትንም የከሰረ ፖለቲካ መስመር ያለርህራሄ ሳይታክት እስከ መጨረሻው ያጋልጣል::

ሆኖም ማህበራችን በነዚህ ሦስት ድርጅቶች ውስጥ በመወናበድ ወይንም በመሳሳት ተደራጅተው ለሚገኙት ቅን ታጋዮች የአብዮቱን ሃቀኛ ኃይሎች እንዲቀላቀሉ ጥሪውን ያቀርባል:: በዚህም ተግላቸው ከጎናቸው ይሰለፋል::



ለ/ ኢማሌድህ፣

የኢትዮጵያ ሃቀኛ ተራማጆች በሕጋዊና ሕገወጥ ትግል ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል::በየጊዜው የአብዮቱን ቀጣይ ችግሮችና መፍትሄዎች እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ለሰፊው ሕዝብ አስጨብጠዋል:: ሰፊው ሕዝብን ከነቀ አድኃሪያን ተጽዕኖ ለማላቀቅ እንዲሁም በግራና በቀኝ አድርባዮች የሚሸረቡበትን ሤራዎች በማጋለጥ ከፍ ያለ ተጋድሎአካሄደዋል:: የማይናቅ ከፍተኛ ድሎች ለሰፊው ሕዝብ አስገኝተዋል::

ሃቀኛ ተራማጆች በየፊናቸው ለኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ከፍ ያለ አገልግሎት አበርክተዋል:: ተገቢ የግንባር ቀደምነት በታቸውን እንዲይዙም ለኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ሕብረት ብዙ አብዮታውያን ታግለዋል፥ ተሰውተዋል:: ይህ ትግል ፍሬ ሰጥቶ በየካቲት ወር 1969 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች የጋራ መርሃ ግብር ባወጡበት ወቅት የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ ይህንን ድል በደስታ ተቀብለውታል::

በአ.ኢ.ተ.ማ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ለእንዲህ ዓይነት የተራማጆች ሕብረትና ለማርክሲስት ሌኒኒስቶች መቀራረብ ከፍተኛ ትግል ሲያካሄድ የቆየ እንደመሆኑ መጠን ሕብረቱን ለመፍጠር የተደረገውን ጥረት በሙሉ ልብ ደግፎ፤ የሕብረቱን አምስት የጋራ አቋሞች ማለትም፣1/ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ዋና ዋና ቅራኔያችና የጊዜው ሁኔታ፣ 2/ ስለወዝአደሩ ፓርቲ አመሠራረት፣ 3/ የዲሞክራሲ ጥያቄ፣ 4/ የመንግሥት ስልጣን ጥያቄ፣ 5/ ስለመለዮ ለባሹ ሠራዊት በማመለከተው በኩል የቀረቡትን ትንተናዎች እንደሚቀበልና ለጋራ መርሃ ግብሩ በስራ መተርጎም እንደሚታገል አስታውቋል:: ሌሎች ተራማጆችም ለዚሁ ዓላማ ኃይላቸውን አስተባብረው እንዲታገሉ ጥሪ ማድረጉ ይታወሳል::

ነገር ግን ለአብዮታዊ ሰደድ ማን አህሎኝነትና ፀረ ዲሞክራሲያዊ አሠራር እንደዚሁም በሌሎች አድርባይ ድርጅቶች አግባቧጅነት የተነሳ ኢማሌድህ በአሁኑ ጊዜ የንዑስ ከበርቴውና የአድሃሪው ቢሮክራሲ ህብረት ተቀጥላና የአብዮታዊ ሰደድ ሌላ መጠሪያ ስም ከመሆን ሌላ ምንም ትርጉም አጥቶ ይገኛል:: በዚህ ሁኔታ የተነሳ የጋራ መርሃ ግብሩም ሆነ የኢማሌድህ የራሱ ደንብ በሚጠይቀው መሠረት በህብረቱ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ውይይት ማካሄድ ፈጽሞ የማይቻልበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል:: የመኢሶንና የኢጭአት ከህብረቱ መውጣት የሚያሳየው ይህንኑ ፀረ ዲሞክራሲ ሁኔታ ነው::

በእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ የኢማሌድህ ወደ ወዝ አደር ሊግ መለወጥ ማለት የሰደድ "ወደ ወዝ አደር ሊግነት" ስም መለወጥ እንጂ ሌላ ትርጉም እንደማይኖረው ገለጸ ነው:: ማህበራችን ይህንን የሰደድ ፀረ አብዮት ሴራ እያወገዘ እያጋለጠና እየታገለ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች እንዲህ ዓይነቱን የንዑስ ከበርቴ ብልጣ ብልጥነት ሳይታክቱ እንዲያጋልጡና በበኩላቸው በየካቲት 1969 ዓ.ም. ባፀደቁት መርሃ ግብር ላይ የሚፈፀመውን የአድርባዮች ክህደት እንዲያወግዙና እንዲታገሉ ሃቀኛ የወዝ አደር ሊግ ለመመስረት የሚያደርጉትን ጥረት እንዲያፋፍሙ በዚሁ አጋጣሚ የንዑስ ከበርቴው ቀኝ ክንፍና አድኃሪው ቢሮክራሲ የፈጠሩትን ፀረ ህዝብ፣ ፀረ፣ አብዮትና ፀረ ወዝአደር ሕብረት "በወዝ አደር ሊግ" ስም ለማወናበድ የሚያደርጉትን ሸርጉድ ካሁኑ በበለጠ ማጋለጥ እንዲጀምሩ ጥሪውን ያቀርባል::

5/ ተራማጅ ድርጅቶች፣ ወጣቶችና ሴቶች፣

ሀ/ የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ / መኢሶን/

መኢሶን ሐቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅት ነው:: የኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት በመታገል፣ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ከዳር እስከዳር በንቃት በድርጅትና በትጥቅ ጉዳና በህዝባዊ አመጽ ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ይችሉ ዘንድ በቆራጥነት የታገለና የሚታገል ድርጅት ነው:: በዚህ ትግሉ በብዛት ህጋዊ መድረኮችን በመጠቀምና በ"አብዮታዊ ሂስ" ማሌያዊ አቋሙ መሠረት ለአብዮቱ ብዙ የማይናቁ ድሎችን እንዳስገኘ እውቅ ነው:: ገና ከለጋነቱ አብዮቱን ለመቀልበት ኢ.ህ.አ.ፓ ከፍተኛ ውቸንበር በፈጠረበት ጊዜ፣ መኢሶን በግንባር ቀደምትነት ከኢ.ህ.አ.ፓ ጋር የርዕዮተ ዓለም ትግል በማድረግ ኢህአፓን ሠፊው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲተፋው ለማድረግ በቅቷል:: ዛሬም ቢሆን ትግሉን የበለጠ አጠናክሮ ቀኝ አድርባዮችን በርዕዮተ ዓለም ደረጃ በበቂ እጋለጧቸዋል::እያጋለጣቸውም ነው::በዚህ ብቻ ሳይሆን የዛሬ አድርባዮች ለጥቅማቸው ብለው ከቱ እንደ በጊዜው "ማርክሲስት ሌኒኒስት" ተብለው ከወጡት ድርጅቶች ጋር ህብረት ፈጥሮ ከዚያም ወደ ውህደት ለመሸጋገር ታላቅ ጥረት አድርጎ ነበር:: ለጠቀኛ ተራማጆች ህብረት ጥሪ ከማድረግና ከመታገል ወደ ኋላ ያለበት አንድም ጊዜ የለም:: ነገ የተባለው ህብረት በዲሞክራሲያዊ አሠራር ለመስራት የማያስችልና የህብረቱ አባላት ከጊዜ ወደ ጊዜ የመደብ ስጋቸው እየሣባቸው ወደ ሰፊው ሕዝብ ወገን ከመጠጋት ይልቅ ወደ አጕብጓጅነት ስለተለወጡ፣ ከአድሃሪው ወገን የተሠነዘረበት ጥቃት እስኪ ደረጃ ላይ በመድረሱ አብዮታችን ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት ከገባበት ከ1969 አጋማሽ ወዲህ ህጋዊ የትግል መስኩ እየመነመነና እየጠበበ በመሄዱ አብዮቱንና አገሪቱን ከገቡበት የፓለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ውጥረት ውስጥ ለማውጣትና



የሚሏቸውን አብዮቱ የሚያቀርባቸውን የዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እሁኑኑ፣ የብሄረሰቦች፣ የፀረ ቢሮክራሲ ትግል፣ የሐቀኛ የወዝአደር ሊግ አመሠራረት፣ የሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር፣ የብሄራዊ ነፃነት...ወዘተ ጥያቄያች መልሳቸው የሚገኘው በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምና በየካቲቱ መርሃ ግብር ነው በማለትና ለነርሱም በስራ መተርጎም የሰፊውን ሕዝብ ወገንነት በመምረጥ በይፋ በህጋዊ ሥራ ያሰማራቸውን አንዳንድ አባላቱን ወደ ህቡዕ የትግል ስልት አዛውሯል:: ይህም ድርጊቱ ፍጹም ትክክለና የማሌ መርሆችን የተከተለ በመሆኑ ማህበራችን ደገፍታል:: ዛሬም በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም ድጋፉን ያድስለታል::

መኢሶን እስከዛሬ በከፍተኛ መስዋዕትነትና ቆራጥነት ሲታገልም ቀሉ የደረገ ቀኝ ክንፍና የቀኝ አድርባዮች በድርጅቱ ላይ ትልቅ ጉዳት አድርሰውበታል:: ድርጅቱ በአብዮቱ ውስጥ የሰጠውንና የሚሰጠውን አብዮታዊ አስተዋጽኦች በመረዳት ይህንን አስተዋፀኦ ሊቀጥል የሚችለው የህቡዕ መዋቅሩን አጠናክሮ ለአብዮቱ ከፍተኛ ድል ሲታገል ብቻ ስለሆነ በዚህ በኩል ከመቼውም ይበልጥ እንዲታሰብበት ማህበራችን ያስገነዝባል::

ድርጅቱ ካደረገው የትግል ስልት ለውጥ በኋላ የጊ.ወ.አ.ደርግ በመኢሶን ላይ የወሰደውና የሚወስደው የማሳደድ የማሰርና የመግደል ዘመቻን ማህበራችን አጥብቆ ይቃወማል:: ጊ.ወ.መንግሥት ከለየላቸው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላቶች ጋር በማበር በድርጅቱ አባላት፣ ወዳጆችና ደጋፊዎች ላይ የማሰር፣ የማፈንና የመግደል ዘመቻውን በአንድ በኩል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቱ አንስቶ የሚታገልላቸው ገለጸና ቁጠባዊ መርሆችና የለት ተለት ተግባር እየታየ ድርጅቱን ኢሳይንሳዊ በሆነ ትንተና "ፈርጣጭ" "ቀኝ መንገደኛ"... ብሎ መወንጀሉን ማህበራችን ፍጹም አይቀበለውም:: የድርጅቱ የትግል ዘዴና በተግባር ለማዋል የሚያደርገውን ጥረት፣ ከሰፊው ህዝብ ጋር ለመቀላቀል የሚያደርገውን ጥረት ስንመለከት መኢሶንን "ቀኝ መንገደኛ" አድርባይ ድርጅቶች "ግራ" ለመምሰል የሚያደርጉት ጥረት ፍጹም ስህተት ነው ብሎ ጉባኤው ያምናል:: ይህንንም ከዚህ በመነሳት ይህ ጉባዔ በድርጅቱ ላይ የሚካሄደውን ጥቃት ለአለም ተራማጆች ለማሳወቅ ቃል ይገባል::

ደርግና አድርባይ ድርጅቶች እስከዛሬው ዕለት ድረስ የድርጅቱን የፖለቲካ መስመር ለመምታት ምንም አይነት ቅስቀሳ ቢያደርጉም ፍጹም አልተሳካላቸውም:: እነሱ የሚያደርጉት ቅስቀሳ የህዝቦችን ቁጣ እተረፈባቸው እንጂ እንዳሰቡት አልሆነላቸውም:: እነሱ በስልጣን ተምክህተኝነታቸውና በአድሃሪነታቸው የሚያካሂዱትን ሰፊው ሕዝብ ከዕለት ወደ ዕለት እየተገነዘበው የሄደና የመኢሶንን የፖለቲካ መስመር የሚያራምዱ መሆኑን ጉባዔው ያምናል::

ሥልጣን የጠማቸው ኢጆንት ፕሮቮከተሮች አገብጋጆች አንዱ" ቀይ ፋና" ሌላ ጊዜ "ህዝባዊ ክንፍ" በማለት የመኢሶን ተገንጣይ "ገራፆች" ነን በለው ቢፍጨረጨሩም የሚያሳዩት ገጽ ከአድርባይነት ሌላ ምንም ስላልሆነ በሚፈጽሙት ፀረ አብዮት ሴራ ማህበራችን ያወግዛቸዋል:: እንደዚህ ያሉትን አወናባጆችን ካለርህራሄ ይታገላቸዋል:: እንዲሁም የሚፈጽሙትን የጥቀማ ሥራ ይከንናል::

በመጨረሻም መኢሶን በለሳኑ በሰፊው ህዝብ ዴምጸ ያደረጋቸውንና የሚያደርጋቸውን በአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረቱትንና እጅግ ጠቃሚነታቸውንና አስፈላጊነታቸውን ጉባዔው ሙሉ ለሙሉ ካመነ በኋላ በተለይ ከቁጥር 64...66 ያደረጋቸውን አብዮታዊ ጥሪያች ማህበራችን ሙሉ ለሙሉ ይደግፋቸዋል::

ከህዝብ ወገን ቆመው መታገላቸው እንደወንጀል ተቆጥሮባቸው የታሰሩት የመኢሶን አባላት ደጋፊዎቻቸና ወዳጆች፣ ወዝ አደሮች አርሶ አደሮች መለዮ ለባሾች ወጣቶች ታጋይ ሴቶች የጭቆን በጨረሰበ ታጋዮች፣ የቀበሌ ተጠሪዎች፣ ሰፋኝ ተራማጆች ...አሁኑኑ እንዲፈቱ ጉባኤው አጥብቆ ይጠይቃል:: ለዚሁም ይታገላል::

በአ.ኢ.ተ.ማ. በትግሉ ሜዳ በሰማእታትነት የወደቁትን የመኢሶን ጓዶችና የሌሎችንም አብዮታዊያን የትግል አርማ ይዞ ለመጓዝ ቃል ኪዳኑን በድጋሚ እያደሰ ለመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ ያለውን ሙሉ ድጋፍ ያረጋግጣል:: ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ ዘንድሮም ለዚህ ሃቀኛ ማሌ ንቅናቄ ዓለም አቀፍ አጋሮችና ድጋፎች ለማስገኘት የሚታገል መሆኑን እንደገና ያረጋግጣል::

ለ/ ኢጥአት፣

አብዮቱ ባቀረባቸው አንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ ማህበራችን እስካሁን እንደሚያውቀው ከሆነ ኢ.ጥ.አ.ተ. ለብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አላማና ለማሌያዊ መርሃ ግብር በታማኝነት እስካሁን የፀና ድርጅት መሆኑን ነው::

ጊ. ወ.መንግሥት አድርባይ ድርጅቶችና አድሃሪው ቢሮክራሲ ህብረት ፈጥረው በሚያሳዩት ማንአህሎኝነት ሳይሸበር በአቋሙ እስካሁን በመጽናቱ ማህበራችን አየደገፈው በዚህም አቋሙ የ"የመኢሶን ተባባሪ"፣ "ጠባብ ብሔርተኛ" ... ወዘተ እየተባለ



የሚደረግበትን አድሃሪ ቅስቀሳ ማህበራችን አያወግዝ ከአላአንጻች ፍርሃትና ከህደት ከሃቀኛ ተራማጆች ጋር እንዲተሳሠርና እንዲተጋገዝ እንዲሁም በአቋሙ እንዲገፋበት አብዮታዊ ጥሪ ያደርግለታል::

በቅርቡ ከኢማሌድህ መታገዱ የኢማሌድህን ፀረ ዲሞክራሲያዊነት፣ ከህደትና መንሸራተት በተጨማሪ ይገልፃል:: ይህንንም ፀረ ዲሞክራሲያዊ ድርጊት ማህበራችን እየ ከነነ በኢ.ጥ.አ.ተ. አባላት ደጋፊዎችና ወዳጆች ላይ የሚፈጸመውን የእሥራትና የከትትል ዘመቻ አጥብቆ እያወገዘ፣ ይህ ዘመቻ አሁኑኑ እንዲቆምና የታሠሩት ባስቸኳይ እንዲፈቱ ማህበራችን አጥብቆ ይጠይቃል::

ሐ/ <u>ስለ ወጣቶች፣ ለወጣቶች ጥሪ፣ ስለ ኢሰወን</u>

የኢትዮጵያ ወጣቶች በኢትዮጵያ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ረጅምና አኩሪ የትግል ታሪክ አላቸው፡በተለይ በጨለማው የኃይለሥላሴ ዘመን ባገሪቱ ውስጥ ተራማጅ የፖለቲካ ድርጅቶች ባልነበሩበት ሰዓት የኃይለ ሥላሴን ፋሽሽታዊ አገዛዝ በማጋለጥና የሰፊውን ሕዝብ ጥያቄዎች አንግበው በመነሳት ግንባር ቀደም ትግል አድርገዋል:: ለዚህም የተቀደሰ ዓላማ ሲታገሉ ብዙ ወጣቶች በገፍ ተጨፍጭፈዋል:: የሚወዷትን እናት አገራቸውን ጥለው እንዲሰደዱ ተደርገዋል:: በየወህኒ ቤቱ በመወርወር ኢሰብአዊ ገፍ ተፈጽሞባቸዋል::

ይሁን እንጂ ይህ የኢት. ወጣቶች ትግል ማንኛውም ዓይነት ፋሽሽታዊና አስታቂ እርምጃዎች ሳይገቱት ዛሬ በኢትዮጵያ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ፍሬአማ ውጤት ሊያስይ ችሏል:: የኢት. አብዮት ከየካቲት ጀምሮ እስካሁን ድረስ በተደረገው ትግል ወጣቱ ተለቀ አስተዋጽኦ አድርጓል:: ዛሬም አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ ለሚደረገው ከፍተኛ ትግል የወጣቱ ሚና ዓይነተኛ ቦታ አለው::

የኢት.ወጣት ለህብረተሰቡ ለውጥ ያለውን ፍላጎትና የትግል መንፈስ በመገንዘብና በመረዳት የተለያዩ የፀረ ህዝብ ጠይሎች እራሳቸውን አብዮታዊ አስመስለው በመቅረብ የወጣቱን አብዮታዊ ትግል ፈር በማሳትና በዙሪያቸው ለመሰብሰብ ትንንቅና የተደጋገመ ጥረቶችን አድርገዋል:: በዚህ ርኩስ የፀረ አብዮት ሴራ ላይ በተለይ ኢህአፓ ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ የተጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው:: በሚችን የሚስብና ዓይን የሚማርኩ ባዶና ፀረ አብዮት ፓለቲካዎችን አንግቦ በመነሳት እስከ ተወሰነ ደረጃ ቢሆንም በወጣቱ እንቅስቃሴ ውስጥ ውዥንብሮችን ሊያስፋፋና ብዙ ሃቀኛ ወጣቶችን ሊያባስት ችሏል::

ሀቀኛ የወጣቶች ድርጅት በተለይም ኢሕወገ ውዥንብርን ከወጣቱ ውስጥ ለማጥፋትና በቦታውም ጥራትን ለማስፈን የርዕዮተ ዓለም፣ የፖለቲካ ትግል ከኢህአፓ ጋር በማድረግ ድልን ተቀዳጅቶአል:: ኢሕወገ በልሳኑ በአብዮት ፋና አማካኝነት ባደረገው ቆራጥ ትግል የተነሳ የሀቀኛ ወጣቶች እንቅስቃሴ ከ1968 ዓ.ም. ጀምሮ ትክክለኛውን አብዮታዊ ፈር ሊይዝ ችሏል:: በወጣት ትውልድ ውስጥ እየተገኘ በመሄድ ላይ ባለው ጥራት መሠረት የወጣቱ በኢሕወገ አካባቢ መሰብሰብ ያስደነገጣቸውና ያሳሰባቸው አድኃሪያች ዛሬ አብዮታዊውን ወጣት የፀረ አብዮት ኢላማ አድርገውታል::

በጥርና በየካቲት 1970 ወሮች "በቀይሽብር" ስም ከአድሃሪ ሃይሎች ጋር ተደባልቀ በወጣቱ አብዮታዊ ትውልድ ላይ የተካሄደው ጭፍጨፋ ለዚህ በቂ ማረጋገጫ ነው:: ለዚህ ጭፍጨፋ የጊ.ወ.ደርግ ፣ የቀኝ አድርባዮች ኢህአፓና በርካ ሪሲው በታሪክ ፊት በቀጥታ ተጠያቂዎች ይሆናሉ:: "የቀኝ መንገደኞች" ወይም ኢህአፓዎች ሆናችኋል በሚል የሀሰት ክስ ብዙ አብዮታዊ ወጣቶች ተወግደዋል አብዮታዊነታቸውና በአድርባይነት አለመበረዛቸው ብቻ እንደወንጀል ተቆጥሮባቸው በመንግሥት እስር ቤቶች ተወርውረዋል::እየተወረወሩም ናቸው:: ባንፃሩ እህአፓዎች ከየእስር ቤቱ እየተለቀቁ ናቸው:: በሚደረግባቸው እስቃይ ግፍና በደል የተነሳ ብዙ ወጣቶች የማያምኑበትን ነገር ከፍረሃት የተነሳ እንዲሰሩ ተገደዋል:: ባቋማቸው የጸኑ ብዙ ወጣቶች ተገድለዋል:: ዛሬ ይህ በወጣቱ ላይ የሚደርሰው ጥቃት ምቹ የፀረአብዮት ሁኔታ በመፍጠሩ በወጣቱ ውስጥ ለቀኝ አድርባዮችና ለኢህአፓ ወጣት ክንፍ ማንሰራራት ዋና ምክንያት ሆኗል:: የጊ.ወ.ደርግ በመንግሥታዊ ተፅዕኖውና በቀኝ አድርባይ ድርጅቶች አማካኝነት የወጣቱን አብዮታዊ ትውልድ ለመቆጣጠር ሲል ከሚወስደው የሃይል እርምጃ የተነሳ ከፖለቲካ ዓለም መገለል እንደአማራጭ የወሰዱ ወጣቶች ቁጥር ቀላል አይደለም:: መጠጥና ዝሙት በወጣቱ ውስጥ የጎላ ችግር ሆኖ እንዲታይ ካደረጉት ዋና ምክንያቶች አንዱ ይኸው የጊ.ወ.ደርግ ፀረ አብዮት እርምጃና የቀኝ አድርባዮች ትብብር ሆኖአል:: በተለይ "ትንታግ፣" ደጀገና "ሬቮሊሽናዊ ወጣት" የተባሉት የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች በወጣቱ መሀከል ተገኝቶ የነበረውን ጥራት ለማደፍረስ የሚያደርጉት ጥረትና የሚፈጽሙት ጥቃት ዛሬ ከምንገዜውም ይበልጥ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ይህ ጉባዔ ይገነዘባል:: በመሆኑም በአውሮፓ የአኢተማ 18ኛ ጠ/ጉባዔ የነኝህን የወጣት ቀኝ አድርባይ ድርጅቶች በዚህ በፀረ አብዮታዊ ወጣት እርምጃቸው እያወገዘ ሀቀኛ ተራማጆች እነዚህ አድርባይ የወጣት ድርጅቶች ጋር የፖለቲካና የርዕዮተዓለም ትግል እንዲያደርጉ ጥሪ ያቀርባል:: ለዚህ ለተቀደሰ አላማ ሊሰለፉ ከሚችሉ ሀይሎች ጋር በመሰለፍ የትግል አንድነት እንዲመሰረት ይህ ጉባዔ በጥብቅ ያሳስባል::

አሁንም ቢሆን አብዮታዊ ወጣቶች ለዲሞክራሲ መብቶች መከበርና፣ የውጭ ሃይሎችን ማንሰራራትና የአብዮታችን በውጭ ሃይሎች ጫንቃ ላይ መውደቅን በመቃወም ቆራጥ ትግል በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: ማህበራችን የነዚህን ቆራጥና ታጋይ አብዮታዊ ወጣቶች ትግል በታላቅ አንክሮ በመመልከት ሙሉ ድጋፉን ይሰጣቸዋል:: ያላንዳች ወንጀል በየእሥር ቤቱ የሚማቀቁት ተራማጅ ወጣቶችም በአስቸኳይ እንዲፈቱና በነሱም ላይ የሚደረገው ክትትል በአስቸኳይ እንዲቆም በጥብቅ ይጠይቃል::



በውጭ አገርም በተለይ በአውሮፓ ደርግና አድርባይ ድርጅቶች ስመ ጥሩውን የተማሪ ንቅናቄ ለማተራመስና ለመከፋፈል የሚያደርጉትን አሻጥርና መፍጨርጨር በጥብቅ ያወግዛል:: ብዙ ተማሪዎች ወደ ጉባዔ ስብሰባ እንዳይመጡ የተደረገው አሻጥር የደርግና አድርባይ ድርጅቶችን በበለጠ አጋልጧቸዋል:: በአኢተማ ከኢት.ዮ.ሕዝብ ጎን ሆነው የወደቁትን ጓዶች አርማ በማንሳት ትግሉን እጥፍ ድርብ አድርጎ እንደሚቀጥል ቃል ኪዳኑን በዚህ ጉባዔ እንደገና ያድሳል::

ለወጣቶች ጥሪ፣

በዛሬው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አብዮቱ በከፍተኛ ምስቅልቅል ውስጥ በሚገኝበት ፣ የፀረ አብዮት ኃይሎች እየተጠናከሩ በሚሄዱበት፣ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እየተቀለበሰ በሚገኝበት፣ በቀኝ አድርባይ መስመር አብዮቱ በሚበረዝበት፣ በአብዮቱ ስም የፀረ አብዮት በሚካሄድበት ወቅት አብዮታዊ ወጣቶች ከፍተኛ ታሪካዊ ሃላፊነት አለባቸው::

ዛሬ በቢሮክራሲው፣በደርግና በኢማሌድህ የቀኝ አድርባዮች ትብብር በተቀነባበረ መልክ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱን ትክክለኛና አብዮታዊ ፈር ለማስለቀቅ በሚደረገው ሴራ የወጣቱን ትውልድ የበራዥ ርዕዮተ ዓለም ተሸካሚ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው:: ከዚህ ጋር በማያያዝ በአሁኑ ወቅት በአብዮቱ ስም፣ ሀቀኛ ተራማጆች አገር ወዳጆች ለብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ሥራ ላይ እንዲውል የሚታገሉ ታጋይ ወዝ አደሮች አርሶ አደሮች፣ ሴቶች የጭቁን ብሔረሰብ ታጋዮች ወጣቶች...ወዘተ በገፍ ይጨፈጨፋሉ፣ይታሰራሉ፣ ይታፈናሉ፣፣ በአንፃሩ የወጣላቸው አድሃሪያች ከእስርቤት እየተለቀቁ በአስተዳደር ፣ በገበሬ፣ በቀበሌ፣ በወዝ አደሩ በአጥሪም በህዝባዊ ድርጅቶች አመራር ላይ ተቀምጠዋል:: ይህ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ የአብዮቱ መቀልበስ ሩቅ አይሆንም ስለሆነም ይህ 18ኛው ጠቅላላ ጉባዔ፣ የወጣቱ ትውልድ ዛሬ አድርባዮች የነሱ በራዥ ርዕዮተ ዓለም ተሸካሚ ለማድረግ ለሚያካሄዱበት የማስፈራራት፣ የዛቻ፣ የማታለል ሴራዎች ሳይበገር በቆራጥነት ከሀቀኛ ተራማጆችና ከሰፊው ህዝብ ጎን ቆሞ እንዲታገል፣ ቀደም ኢህአፓ የወጣቱን ትውልድ ፀረ አብዮት ካምፕ ለማስገባት ካደረሰበት ግፍ ተምሮ በጥንቃቄ በትጋትና በቆራጥነት እንዲታገል፣ ለቀኝ አድርባይ ድርጅቶች ለደርግ እንዲያጎበድዱ የሚካሄድበት ልዩ ልዩ ተፅዕኖ እንዲቋቋም፣

የብ.ዲ.ፕሮግራምን ለመቀልበስ የሚደረገውን ሴራ ከሀቀኛ ተራማጆችና ከሰፊው ህዝብ ጎን ቆሞ እንዲታገል፣

በአብዮቱ ወዳጆች ላይ የሚካሄደውን የእስራት፣ የግድያ፣ የጭቆና ሴራዎች በቆራጥነት እንዲታገል፣

ዛሬ የበ.ዴ.አብዮት ፕሮግራምን በተቀበሉና በአፍተቀበለው በከኋት መሀከል በሚካሄደው የመስመር ትግል ከበሚታዩ መንፈስ በራቀ ሁኔታ በጥሞና አጥንቶ ትክክ ለኛውን መስመር እንዲከተሉ፣

ለዘላቂው ትግል ለመዘጋጀት ቆርጦ የማሌን ርዕዮተ ዓለም እንዲያጠና፣

ለዴሞክራሲና ለነፃነት ዴሞክራሲያዊ ነፃነቱ እንዲታገል፣አብዮታዊ ጥሪ ያደር ጋል:: በዚህም ትግሉ ማህበራችን ከጐኑ ይሰለፋል::

ኢሰወን፣

ኢሰወን የኢትዮጵያ ወጣቶች ትግል ከግራና ከቀኝ አድርባይ ፖለቲካ መስመር ራሱን ጠብቆ በትክክለኛው ጎዳና እንዲጓዝ የታገለና የሚታገል አንጋፋ አብዮታዊ የወጣት ድርጅት ነው:: ለዚህም እስከዛሬ ድረስ ከኢሀአፓ፣ ከትንታግ፣ ከደጀንና ከ"ሬቮሉሽናዊ" ወጣት አድርባይ ድርጅቶች ጋር ያደረገውና የሚያደርገው ትግል ዋና ምስክር ነው:: ዛሬ በዚህ አብዮታዊ ድርጅት ላይ የሚወሰደው ጠንካራ የፀረ አብዮት ሴራና እርምጃ ከፍተኛ ቦታን ይዟል:: ይሁን እንጂ ኢሰወን በዚህ ሁሉ የፀረ አብዮት ሴራና ከተተለ ሳይደናገጥ መስመሩን አጥብቆ ማራመዱ መቻሉ የድርጅቱን አብዮታዊነት በይበልጥ ሊያረጋግጥለት ችሏል::

ኢሰወን ምስጢራዊ መዋቅሩን ሳይገልጽ ህልውናውን በይፋ በፕሮግራሙ አማካኝነት ከገለጸበት ጊዜ ጀምሮ በአብዮታዊ ወጣቶች መሀል ታላቅ የትግል ጥንካሬና በአድኃሪዎች ሠፈር ደግሞ ታላቅ መርበድበድ ታይቷል:: ይህ ሀቅ ከኢሰወን አብዮታዊነት በፍጹም ተለይቶ ሊታይ የማይችል መሆኑን ጉባዔ አምኖበታል::በአውሮፓ የኢት. ተማሪዎች ማህበር በ18ኛ ጠ/ጉባዔ ኢሰወን እስከዛሬ በኢት.አብዮት ውስጥ ያራመደውን የፖለቲካ መስመር በመመርመርና ፕሮግራሙን በማጤን በመከራም ዘመን ሀቀኝነቱን ቆራጥ መሆኑን እያረጋገጠና በተጨባጭ እያሳዩ በመሄዱ ላይ ያለ ድርጅት መሆኑን በማየት በተለይም የመኢሶን ወጣት ክንፍ መሆኑን በማወቅ ያልተቆጠበ ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል:: ይህ ጉባዔ ማህበራችን ከዚህ ድርጅት ጋር ሙሉ የትግል ትብብርና አንድነት እንዲመሠረት ያሳስባል::



መ/ ሴቶች፣ /ኢሴአን/

የየካቲት 66 ዓብዮት አይነተኛ ከሚያደርጉት አንዱ ጭቁን ሴቶች በፆታቸው የሚደርሥባቸውን ጭቆና በመቃወም የራሳቸውን ጥያቄ ይዘው በመነሳታቸው ነው:: ጭቁን ሴቶችም ባደረጉት ቆራጥ ተጋድሎ ብዙ ድሎችን ተጎናጽፈዋል:: ከዚህም አንዱ የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ መቋቋም ነው:: ይህ ኮሚቴ ሴቶችን ለማንቃትና ለማደራጀት ቢቋቋምም በኢሀአፓ አድሃሪ ሴቶች በመያዙ ኮሚቴው በቆየበት አንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ምንም ዓይነት ሥራ ሳይሰራ ሊፈርስ ችሏል:: ከዚያም በኋላ የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ዋና ድል የሆነው ብ.ዲ.አ.ፕሮግራም በታወጀበት ወቅት የህዝብ ድርጅት ጊዜያዊ ጽህፈት ቤት በተቋቋመበት ጊዜ የሴቶች ንዑስ ኮሚቴ በመመሥረቱ ሴቶችን በቀበሌ በገበሬ፣ በፋብሪካ ውስጥ ማደራጀት ተጀምሮ ነበር:: ነገር ግን በዓሁኑ ወቅት ደርግ ወደ ቀኝ በመርገጡ የሴቶችንም ጥያቄ እንደተቀረው የህብረተሰቡ ክፍሎች ጥያቄ መልስ አለሰጠበትም፣እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ የሴቶች ድርጅቶች አመራር. በቀኝ አድርባይ ሴቶች እንዲያዙና ማህበሮችም ከእጅ ሥራ ኢግዚቢሽን ፣ ሥንቅ ከማቀበል አላለፉም::

በዚህ በኩል ሴቶች መብታቸውን ለማስከበር በተለይ በፖለቲካ ንቃት በኩል ከፍተኛ ቅስቀሳ ተደርጎ ሴቶችን ለእኩልነታቸው እንዲታገሉ ማድረግ ያሥፈልጋል:: በተለይ በዚህ ሥራ ሲታገሉ በአድሃሪ ጥይት የወደቁትን ጓዶች ሽዋሉል መንግሥቱ፣ አጥናፍ ዓለም የማነ እንዲሁም ሌሎችን ጓዶች በታላቅ ስሜት ያስታውሳቸዋል:: በአሁኑ ጊዜ ጊ.ወ.መንግሥት/ደርግ/ በኢሴአን አባልነትና ደጋፊነት የሚጠረጠሩትን በመረሸንና በማሰር የሚፈጽመውን ፀረ አብዮታዊ ተግባር ይህ ጉባዔ ያወግዛል::

ማህበራችን፣

የታሰሩት ታጋዮች አብዮታዊ ሴቶች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል:: ይታገላል፡

በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚቋቋመው የሴቶች ማህበር ዴሞክራሲያዊ አሠራርና አመራር እንዲኖረው ይጠይቃል:: ይታገላል::

ለኢሴአን ሙሉ ድጋፍ ይሰጣል፡:

ስለ ኢሴአን፣

በ17ኛው ዓመታዊ ጉባዔ ወቅት ማህበራችን ለኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ ሙሉ ድጋፉን መስጠቱ ይታወሳል:: አሁንም የሰጠውን ድጋፉን እያደሰ በኢሴአን አከባቢ የተደራጁት ሴቶች የኢትዮ.ብ.ዲ.አ.ፕሮግራም ፈሩን ሳይስቱ እስከዛሬ ድረስ ያደረጉቸውን ትግሎች ያደንቃል:: ባሁኑ ጊዜ ከዚህ ብ.ዲ.አ.ፕሮግራም የተንሸራተቱት

ደርግና አድርባይ ድርጅቶች /ሰደድ፣ ወዝና ማሌሪድ/ በዚህ አብዮታዊ ድርጅት ላይ የሚያደርጉትን ፀረ አብዮታዊ ሴራ ማህበራችን ያጋልጣል፣ ያወግዛል::

በኢሕአፓ አባልነት ወይም ደጋፊነት እየተመረመረ ደርግና አድርባይ ድርጅቶች የሚያደርሱባቸውን ክትትል እስራትና ግድያ ማህበራችን አጥብቆ ያወግዛል:: የታሰሩት ጠቅላ ተራማጅ ሴቶች እሁኑኑ እንዲፈቱ ማህበራችን ይጠይቃል፣ ይታገላል::

6. <u>አድሃሪ ድርጅቶች፣</u>

ሀ/ <u>ኢ.ዲ.ዩ.</u>፣

ይህ ድርጅት የፊውዳል ርዝራዦች የአድኃሪ ሲቪልና ሚሊተሪ ቢሮክራሲ ክፍል በምዕራብ ኢምፔሪያሊስቶችና የአድሃሪ የአረብ መንግሥታትና ነገሥታት የሚደገፍ ድርጅት መሆኑ ተደጋግሞ ተገልጿል::

ይህ ድርጅት በ1969 ዓ.ም. በትጥቅ ትግል ጭምር በተለይ በጎንደር ክፍለ ሃገር በመንቀሳቀስ በአብዮታችን ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሷል:: በውስጥ ከፍተኛ የሆነ የቢሮ፣ የጠርና የንግድ አሻጥር ሠርቷል:: አሁንም ይሠራል:: የኢሀአፓን ፀረ አብዮት ሤራዎችና ግድያዎች በብዙ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ መንገዶች በማገዝና በመሸፈን ረድቷል አሁንም ይረዳል:: ይህ ድርጅት ዛሬ <u>በውስጥ</u> በተለይ ከጎንደሩ ጦርነት በኋላ ቢያሽገሽግና ቢዳከምም <u>በውጭ</u> ከአድኃሪ ኃይሎች ጋር ተባብሮ በመስራት አብዮታችንን በመፈታተን ላይ ያለ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ቀንደኛ ጠላት ነው:: ማህበራችን ይህን አድኃሪ ድርጅት አጥብቆ እያወገዘ ያለ ርህራሄ ያጋልጣል፣ ይታገላል::

ለ/ <u>ኢ.ሀ.አ.ፓ.</u>፣

ይህ ድርጅት ከመጀመሪያው ጀምሮ በተሳሳተ የፖለቲካ መስመር ላይ የተመሰረተ ድርጅት ሲሆን እስከ1969 ዓ.ም. ብዙ የተወናበዱ የመስመሩ ተከታዮች ሊያገኝ ችሎ ነበር:: በ1968/69 ብዙ ሃቀኛ ታጋዮችን ረሽኖዋል:: የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በከንቱ አስጨፍጭፏል::

ከየካቲት መጋቢት 1970 የተካሄደው "ቀይ ሽብር" ቢያዳክመውም በዚህ ቀይ ሽብር እንቅስቃሴ የተመታው ገፋ ቢል የደለው ክፍል ብቻ መሆኑ ገለጸ ነው:: ኢሀአፓ ባሁኑ ጊዜ አንድ ድርጅት በሳለ ተደመሰሰ አይፍጠ ይገኛል::



የዘራቸውን "የኢማሌድህ" አባል ድርጅቶች በመበርበር ላይ ሲሆን በዚህም አሰራሩ የኢማሌድህ ድርጅት አድርባይነት እጅግ አመቺ የሆነ ሁኔታ ፈጥሮለታል:: ባሁኑ ወቅት ይህንን በመጠቀም በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ለማንሠራራት ዕድል አግኝቷል:: ለዚህም ተጠያቂዎች "የኢማሌድህ" አባል ድርጅቶች ናቸው::

የነዚህ ድርጅቶች የመደብ መሠረት የገዢ ከበርቴው መደብ ቀኝ ክንፍ ሲሆን ይህ ክፍል ባሁኑ ጊዜ በአብዮት ስም ለፀረ አብዮት በመሥራት ላይ ነው:: ባንድ በኩል ድምፁን አጥፍቶ በጥብቅ ተደራጅቶ ፀረ አብዮት ሤራዎችና አሻጥሮችን፣ በሌላ በኩል "ከነፍስ ወከፍ ደረጃ" በኢማሌድህ ድርጅቶች ውስጥ ተደራጅቶ በግልጽ ፀረ አብዮት እያካሄደ ነው:: እንደዚሁም ከደርግ አገዛዝና ከአድር ባይ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በፀረ መኢሶን አቋም እጅና ጓንት ሆኖ በመሥራት ላይ ይገኛል:: አሁንም የኢዲዩ የቢሮክራሲውና የኢምፔሪያሊስቶች አፈ ቀላጤ ድርጅት ነው:: በውጭም ከቀንደኛ ኢምፔሪያሊስቶችና ከገበሬ አበር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የኢትዮጵያን ጭቁን ህዝብ ትግል በማጥላላት ከፍ ያለ ዘመቻ ሲያካሄዱ ቆይቷል:: አሁንም ያካሄዳል::

ማህበራችን ይህን ፋሽስታዊ ድርጅት ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ ፀረ ኢሀአፓ ትግሉን ይቀጥላል::

## 7. ስለ ብሔረሰቦች ጥያቄ፤

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ብሔረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያላቸውን መብት ያለማወላወል የሚያውቅ መሆኑን ከዚህ በፊት ደግሞ ደጋግሞ አረጋግጧል:: አሁንም ያረጋግጣል::

### ሀ/ ስለ ኤርትራ፤

የኤርትራ ችግር ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኘው ከኢትዮጵያ አብዮት ግብ መምታት ጋር እንደሆነ ግልጽ ነው::ይህን ችግር በሰላም ለመፍታት የቀረበውን የግንቦት 8 ቀን 1968 ዓ.ም. ባለዘጠኝ ነጥብ ፖሊሲ ማህበራችን ደግፏል፤ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የዲሞክራሲን መብት አፍኖ በመያዙ፤ ይህ የሰላም የፖለቲካ መፍትሄ በሥራ እንዳይተረጎም እንቅፋት በመሆኑ፤ከፖለቲካው መፍትሄ ይልቅ ፤ወታደራዊ ኃይል በመጠቀሙ ብዙ ጭፍጨፋ በጥቅሉ የኤርትራ ሕዝብ ላይ ደርሷል:: በአኢተማ ይህ የኤርትራ ጥያቄ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ያለአንዳች የውጭ ተፅዕኖ እንዲፈታ በኤርትራ ጭቁን ሕዝብ ውስጥ ተራማጆች ቅስቀሳ ለማድረግ ይችሉ ዘንድ የዲሞክራሲ መብቶች ባስቸኳይ መለቀቅ እንዳለባቸው ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል::

በአሥራ ሰባት ዓመት ትግል ጊዜ በ29/6/78 በቤይሩት ከተማ የሁለት ግንባሮች ተጠሪዎች ባደረጉት የጋራ ፕሬስ ኮንፈረንስ ላይ ያላንዳች ፕሪኮንዲሽን ለመደራደርና ዲሞክራሲያዊ መፍትሔ ለመሻት ያደረጉት ጥሪ አንድ እርምጃ ወደፊት በመሆኑ

1ኛ/ የኤርትራ ግንባሮች በዚህ አቋማቸው እንዲፀኑ የወንድማማች ደም መፍሰስ ቆሞ ድርድር እንዲከፈት፤

2ኛ/ ጊ.ወ. መንግሥት የኤርትራ ግንባሮች ያደረጉትን ጥሪ ተመልክቶ የሚፈለገበትን አስተዋጽዖ እንዲያደርግ፤

3ኛ/ የኤርትራ ጭቁን ሕዝቦችና ሃቀኛ አብዮታዊያን ከተቀረት የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦችና አብዮታውያን ጋር ትግላቸውን እንዲያስተባብሩና እንዲያቀናጁ በአ.ኢ.ተ.ማ. የ18ኛው ጠቅላላ ጉባዔ አብዮታዊ ጥሪ ያቀርባል::



### ለ/ የትግራይ ሕዝባዊ ነፃ አውጭ ግንባር፤

የትግራይ ሕዝባዊ ነፃ አውጭ ግንባር ከሚያካሂደው የትጥቅ ትግል ሌላ ፕሮግራሙንም ሆነ ዓላማውን ለማሳወቅ ብዙ ቅስቀሳ ባለማድረጉ አቋሙ በተረጋገጠ ሁኔታ ሊታወቅ አልቻለም:: ይህን ጉዳይ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው በዓመቱ ውስጥ እንዲከታተል ይህ ጉባዔ ወስኖታል:: የትግራይ ሕዝባዊ ነፃ አውጭ ግንባር የብ.ዲ.አ.ፕሮግራም የሚቀበል፤ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ የትግራይን ሕዝብ የዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ለማስከበር የሚታገል፤ ዲሞክራሲያዊ የብሔረሰብ ንቅናቄ ከሆነ በአ.ኢ.ተማ ድጋፉን እንዲሰጠው የ18ኛው የአ.ኢ.ተ.ማ. ጠቅላላ ጉባዔ ወስኗል::

### ሐ/ የአፋር ብሔረሰብ እንቅስቃሴ፤

በአኢተማ 18ኛ ዓመታዊ ጠቅ/ጉባዔ ከዚህ በፊት ለአፋር ብሔረሰብ ንቅናቄ የሰጠውን ድጋፍ ያድሳል:: ይህ ንቅናቄ ያቀረበውን የሬፈረንደም አውቶኖሚ ጥያቄ ይደግፋል::

ሬፈረንደም አውቶኖሚ በማለት ደርግና የቀኝ አድርባዮች በለፈፉም ግልጽ የሆነው የአፋር ብሔረሰብ ጥያቄ እስካሁን መልስ አላገኘም፡፡በዚህ ረገድ ማህበራችን ደርግ በሥራ ላይ እንዲያውል በብ.ዲ.አ.ፕሮግራም ውስጥ የሰፈረውን የሬፈረንደም አውቶኖሚ ጥያቄ ለአፋር ብሔረሰብ ባስቸኳይ ሥራ ላይ እንዲውል ይጠይቃል::

የአፋር ብሔረሰብን ንቅናቄ በተንኰል በሥልጣን ትምክህት በቁጥጥር ሥር ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት ያወግዛል፤ የአፋር ብሔረሰብ ንቅናቄ ከደርግ ቁጥጥር ነፃ እንዲሆን መታገል እንዳለበት ያሳስባል፤ የአፋር ብሔረሰብ ጭቁን ሕዝቦችና ሃቀኛ ተራማጆች ትግላቸውን ከኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦችና ሃቀኛ ተራማጆች ጋር በበለጠ እንዲያስተባብሩና እንዲያቀናጁ በአ.ኢ.ተ.ማ የ18ኛ ዓመታዊ ጉባዔ ጥሪውን ያቀርባል::

### መ/ የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር፤

በደቡብ ኢትዮጵያ የትጥቅ ትግል የሚያካሂደው የኦሮሞ ነፃ አውጭ ንቅናቄም ዓላማውን ለማሳወቅ ብዙ ቅስቀሳ አላካሄደም:: ስለሆነም አቋሙ በተረጋገጠ ሁኔታ ሊታወቅ አልተቻለም:: ይህንን ጉዳይ መጭው ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ በዓመቱ ውስጥ እንዲከታተል አደራ ሰጥቶታል:: የኦሮሞ ነፃ አውጭ ንቅናቄ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መሠረት የብሄረሰቦች እኩልነት ታውቆና ተረጋግጦ ለምትመሠረት ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የሚታገል ከሆነ ማህበራችን ድጋፉን ይሰጣል::

ሰ/ "የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጭ ግንባር" ከሚባለው አሻንጉሊት ድርጅት፤

ሶማሊያ የኢትዮጵያን አንድ አምስተኛ መሬት ቆርሳ ለመውሰድ ባላት ከንቱ የመስፋፋት ፓሊሲ "ከምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጭ ግንባር" በተሰኘው አሻንጉሊት ድርጅት አማካይነት የዚህን ድርጅት ቀጥረኞች እያሰለጠነችና ወደ ኢትዮጵያ እየላከች አብዮታችንን ክፉኛ ተፈታትናለች አሁንም እየተፈታተነች ነው። መደበኛ ጦርን በማሰለፍ ግልጽ የሆነ ጦርነት ከፍታ የኢትዮጵያን ግዛትና ሕልውና ደፍራለች። ጭቁኑን ሕዝብ ጨፍጭፋለች። ይህ ነው የማይባል ጉዳት በንብረት ላይ አድርሳለች። በአ.ኢ.ተ.ማ. 185ኛ ጠ/ጉባኤ ሶማሊያ በሃገራችን ላይ ያደረገችውን ወረራ አጥብቆ ያወግዛል። ይህን "የምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጭ ግንባር" የተሰኘውን አሻንጉሊት ድርጅት አጥብቆ ያወግዛል።

ማህበራችን የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የሶማሊያን ወረራ ለመከላከል ያደረጉትን መራራ ተጋድሎና ያስገኙትን ድል ያደንቃል።

የሶማሊያ መንግሥትና አድኃሪው ቢሮክራሲ በምሥራቅና በደቡብ ምሥራቅ የኢትዮጵያ ህዝቦች ላይ ያደረሱትንና የሚያደርሱትን ጭፍጨፋ በአኢተማ 185ኛ ጠ/ጉባኤ አጥብቆ ያወግዛል።

ደርግ የአድኃሪው ሲቪልና ሚሊቴሪ ቢሮክራሲ ለዘመቻው በሰጡት ፀረ ሕዝብ አድኃሪ አመራርና ባደረጉት አሻጥር በህዝቡና በተዋጊው ጦር ላይ ያደረሱትን ጥቃቶች ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንጊዜም ከአእምሮው አይረሳም።

በዚሁ አንፃር፤

1. የብሔረሰቦች ሙሉ መብት እንዲታወቅ ዲሞክራሲ መብቶች እንዲለቀቁ፤
2. ሶማሊያ የኢትዮጵያን ድንበር እንደምታከብር በይፋ እንድታስታውቅ፤
3. ሁሉም ወገኖች ፕሮፓጋንዳቸውን እንዲያቆሙ፤
4. ሶማሊያ የኢትዮጵያን ድንበር ካከበረች ሁለቱም ወገኖች የጦር ክምችት እንዲያቆሙ፤
5. ችግሩን በአፍሪካ አንድነት ቻርተር መሠረት ውይይት አድርገው በሰላም ለመኖር ጥረት እንዲያደርጉ፤ ማህበራችን ያሳስባል።



ረ/ ስለ ሌሎች ብሔረሰቦች፤

ባሁኑ ወቅት፤ በኤርትራ፤ በትግራይና በአፋር ከሚታወቁት የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎች በተጨማሪ ዛሬ በተለይም በደቡብ ክፍለ ሃገር ያሉት ብሔረሰቦች በብሔረሰቦቻቸው ጥያቄዎች አካባቢ እየተሰበሰቡና እየተደራጁ ናቸው።

እነዚህና ሌሎች ብሔረሰቦች ለእኩልነታቸው፤ ለመታገል የሚያደርጉትን ጥረት ማህበራችን እየደገፈ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ውስጥ ተገቢ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይህ ጉባኤ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል።

ከዚህ በፊት ለኦሮሞ ሕዝቦች እኩልነትና ዲሞክራቲክ መብቶች የሚታገለውን የኦሮሞ ብሔረሰብ ዲሞክራቲክ ንቅናቄ /ኦብዲን/፤ እንዲሁም የሃዲያ ብሔረሰብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ማህበራችን የሰጣቸውን ድጋፍ እያደሰ፤ ከብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፈር ሳይለቁ ትግላቸውን እንዲያካሄዱና ተገቢ አስተዋጽኦአቸውን እንዲያደርጉ ይህ ጉባኤ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል።

8. ስለህዝባዊ ድርጅቶች፣

ህዝባዊ ድርጅቶች በወዛደሩ መሪነት ወደፊት ለሚቋቋመው ሕዝባዊ መንግሥት መሠረቶች ናቸው:: የነዚሁ ድርጅቶች መጠናከር ማለት ይህንን ሕዝባዊ መንግሥት ለማቋቋም የሚደረገውን ትግል ማፋፋምና ማፋጠን ማለት ነው:: የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራጅተው በአብዮቱ ላይ የሚያካሂዱትን ዘመቻ ለመቋቋምና በማያዳግም ሁኔታ ለመደምሰስ በሉም ለአ.ኢ.አ.ገበ መምታት የሕዝባዊ ድርጅቶች መጠናከር መስፋፋትና ነፃ እርምጃ መውሰድ ከፍተኛ ዋበትና ነው::

የየካቲት አብዮት ከተገኙ ፀፋቸው ድሎች አንዱ የሰፊው ሕዝብ ድርጅቶች በመላው ኢትዮጵያ መፍለቅለቅ ነው:: ለዚህም የወዛደሩ ማህበራት፣ የገበሬ ማህበራት፣ የቀበሌ ማህበራት፣ የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች፣ አብዮታዊያን የሴቶች ድርጅቶችና የአብዮታዊያን ወጣቶች ድርጅቶች ወዘተ ምስክሮች ናቸው:: እነዚህን ድርጅቶች ለማቋቋምና ለማጠናከር ሀቀኛ ተራማጆች ከፍተኛ መስዋዕት ከፍለዋል። ለዚሁ አብዮታዊ ግዳጅ ተሰማርተው የነበሩ ታጋይ ወዛደሮች አርሶ አደሮች፣ ወጣቶች ሴቶች ምሁራኖች ወዘተ በኢሀአፓ በኢዲዩና በአድሃሪያን ነፍሰ ገዳዮች በየቦታው ተረሽነዋል:: በእንደዚሁ ዓይነት ከፍተኛ መስዋዕት በአያሌ ታጋዮች ደም የተመሰረቱት ህዝባዊ ድርጅቶች በአለተሟላ ዝግጅታቸውና በመጠነኛ ነፃነታቸው አገሪቷ አብዮቱን ወደፊት ለመግፋት በሚወስዱት እርምጃ ምድረ አድሃሪያን አርበብተዋል::

በአሁኑ ወቅት አብዮቱ የደረሰበት ደረጃ የሚጠይቀው የነዚህን ህዝባዊ ድርጅቶች በበለጠ መንቃት መደራጀትና መታጠቅ በመሃላቸው ሊኖሩ የሚችሉትን ንዑሳን ቀራኒዎች በማቻቻል በጠላቶቻቸው ላይ እንደ አንድ ሰው ሆኖ በመነሳት ነፃ እርምጃዎችን ከምን ጊዜም በበለጠ ማፋፋም ሆኖ የበሰበሰው ቢሮክራሲ ፀረ ዲሞክራቲ ደርግና ሰፊውን ሕዝብ ለጊዜያዊ ጥቅም የሸጡ አድርባዮች / ወዘተ፣ ሰደድና ማሌሪድ/ እያፈረጧቸው የራሳቸው ተቀጥላ እያደረጓቸው፣ ድርጅታዊ ህልውናቸውን እየነፈጓቸውና ዲሞክራሲያዊ እርምጃቸውን እያጨናገፉባቸው ናቸው::

ስለሆነም መጪው ትግል የፈረሱትን ህዝባዊ ድርጅቶች መልሶ ለማቋቋምና ለማጠናከር፣ ህዝባዊ ድርጅቶችን የደርግ፣ የቢሮክራሲ፣ የአድርባዮች ተቀጥላ ለማድረግ የሚካሄደውን ሴራ ለመቋቋም ባጥር ቃል የህዝባዊ ድርጅቶችን ነፃ ዲሞክራሲያዊ ህልውና ለማስጠበቅ መሆን ይኖርበታል::

ሀ/ የሠራተኛ ማህበሮች፣

ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ሃቀኛ ወዛደሮች በሕጋዊ መንገድ ተሰማርተው የመሥራት ዕድላቸው እጅግ እየመነመነ ሄዷል:: በመንግሥትና በአድርባዮች ድርጅቶች ትዕዛዝ ብዙ ታጋይ ወዛአደሮች እየተለቀሙ በመታሰር ላይ ናቸው:: ይህንንም ሁኔታ በማ የቀደሞ የኢሀአፓ አባሎች ሂስ አድርገዋል እየተባለ በአመራር ቦታ እየተተኩ ሄደዋል::



እሁን በተያዘው "ቀኝ መንገደኛ" በሚል ፈሊጥ የፈጠራ ክሶች በመመስረት በአብዮቱ የተፈተኑ ታጋዮች ከሥራ ቦታቸው እየተወገዱ የአድርባይ መሥመር አስተጋቢዎች እየተኳቸው ናቸው:: ጊ.ወ.መንግሥት በአድርባይ ድርጅቶች እየታገዘ የወዛአደሮችን ወካዮች እያጠመደ ለፍላጎቱ እንደሚያመቸው እያሳካ በዚና ማስራጪያች ማስተጋባት ሥራ ብሎ ይዟል:: ለዚህም ተግባር ያመቹ ዘንድ የወዛአደር መሰፍኖችን ለመኰትኰት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው:: የሠራተኛ ማኅበሮች ራሳቸውን የቻሉ ከቢሮክራሲው ቁጥጥር ውጪ የሆኑ ነፃ ድርጅቶች መሆናቸው ቀርቶ ወደ መንግሥት ድርጅት አካልነት በመለወጥ ላይ ይገኛሉ:: ስለዚህም ነፃና ዲሞክራሲያዊ ሕልውናቸውን እያጡ ናቸው:: በዚሁም የተነሳ ሰፊው ወዛአደር ከማህበሮቹ እንዲሸሽ ተገዷል::በመንግሥቱ የተያዘው ፖሊሲ እነዚህን ማህበሮች ወዛአደሩን የመቆጣጠሪያ መሣሪያ ለማድረግ እንጂ ለመብቱና ለዘላቂ ጥቅሙ የሚሰበሰቡትና የሚያታግሉት ድርጅቶች መሆናቸው እየቀረ እንደሄደ እየተረጋ ነው:: ይሁንና ሀቀኛ ተራማጆች ይህንን ሁኔታ እያጋለጡና አብዮቱ ትክክለኛውን ፈር መልሶ እንዲይዝ የሞትና የሽረት ትግል በማድረግ ላይ ናቸው:: ስለዚህም አድርባዮችና ፀረ አብዮት ኃይሎች ተንኮላቸውን አገጡ እንዳያደርሱ እንቅፋት በሆኑዋቸው ሀቀኛ ተራማጆች ላይ የሚያካሂዱት ከፍተኛ ጥቃና እየከፋ መጥቷል::

ማህበራትን ለነዚሁ ኃቀኛ ተራማጆች የማያወላውል ድጋፋን እያደሰ በእስር ላይ የሚገኙት ታጋይ ወዛአደሮች ባስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል:: በዚህም አጋጣሚ ታጋይ ወዛአደሮች በጥንቃቄና በትጋት ከማናቸውም የመንግሥት ተፅዕኖ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ለሆኑ የሠራተኛ ማህበሮች መቋቋም እንዲታገሉ ጥሪ ያቀርባል:: ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ እንደታየው ሁሉ መንግሥት ከአድርባይ ድርጅቶች ጋር እየተባበረ ስለሆነ ነፃ የሆኑትን የሠራተኛ ማህበሮች የሚያፈራርሰው፣ ይህን ድርጊት ለመቋቋም ታጋይ ወዛአደሮች ትግላቸውን ከሀቀኛ ተራማጆች ጋር እንዲያጠምሩ ይህ ንቢዓ ጥሪውን ያቀርባል::

ለ/ መኢሰማ፣

በቀደሞው ፊውዳል ቡርዧ ሥርዓት ውስጥ የኢምፔሪያሊስቶችንና የፊውዳሉን መደብ ጥቅም እንዲያስጠብቅ በሠራተኛው ጫንቃ ላይ ተጭኖ የነበረውን ኢሰአማ አፍርሶ በቦታው በአ.ኢ.አ. ሂደት ጊዜ የሠራተኛውን ጥቅም የሚያስከብር አዲስ የሠራተኛው የሙያ ማህበር መኢሰማ እንዲቋቋም ሀቀኛ ተራማጆችና ወዛአደሮች ከፍተኛ ትግል ማድረጋቸው ይታወሳል:: ቢሮክራሲውና ደርግ ይህንንም ድርጅት በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ በየጊዜው ያደረጉትን ሙከራ ተቋቁሞ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ህልውናውን ለማስጠበቅና ለማስከበር ከፍተኛ ትግል ተደርጓል:: በዚህም ትግል ብዙ መስዋዕት ተከፍሏል::

ነገር ግን በየጊዜው የተቀነባበሩ ሴራዎችና አሻጥሮች ሠራተኛውን እንዳላንገራገሩት የተረዳው ደርግ ያለወዘደረ ተከታትሎ በገሃዱ ፀረ ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መጋቢት 19 ቀን ህጋዊውን አሠራር በጉልበት ሽሮና በሠራተኛው ተመርጠው የነበሩትን መሪዎች : እስር ቤት አጉሮ በምትካቸው በማንአለብኝነት የራሱን አሻንጉሊቶች ሾሞበታል:: በዚህም ዓይነት ዛሬ የመኢሰማ አመራር በቀኝ አድርባዮችና በኢህአፓ አባሎች እጅ ወድቋል:: በዚህም የተነሳ ወዛደሩ አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ በገጠሙት ሌሎች ችግሮች ላይ "በእንቅርት ላይ...." ሌላ መራራ ትግል ተጭኖበታል:: ዛሬ የወዛደሩ ቤት እንደ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የመንግሥት መሥሪያ ቤት እንጂ ወዛ አደሩ ለጥቅሙ የሚታገልበት ነፃ ድርጅት መሆኑ ቀርቷል::

መጋቢት 17 በመኢሰማ ውስጥ የተደረገው ሹም ሽር የዛሬ ደርግና አባሪዎቹ አድርባይ ድርጅቶች ለወዛ አደሩ ያላቸውን ንቀት በገሃዱ ያሳዩበትና በነሐሴ 1955 ዓ.ም. ኃይለ ሥላሴ በኢሰአማ ውስጥ ያደረገውን ሹም ሽር በትክክል የሚያንፀባርቅ ድርጊት ነው:: ለወዛደሩ ቆመናል በማለት በአደባባይና በዜና ማሰራጫዎች ቢምሉና ቢገዝቱም ቃሉ እነዚህ አድር ባይ ንዑስ ከበርቴዎች ፍላጎታቸው ወዛአደሩን ለድርጅታቸው ተቀጥላ ለማድረግ እንጂ የወዛአደሩን ዐውነተኛ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ማህበር እንደሚፈሩ በገሃዱ አሳይተዋል:: አብዮቱ ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ባካሄደው ትግል እንደተመሰከረው ሁሉ ለወዛደሩ ዐውነተኛ አርነት ነፃና ዲሞክራሲያዊ የሆነ ማህበር ያለውን አስተዋጽኦ በመረዳት ይህንን ማህበሩን መልሶ ለማቋቋም እንዲታገል ማህበራችን ጥሪ ያደርጋል /ኢ.ወ.መ/ደርግና አድርባይ ድርጅቶች "ቀኝ መንገደኛ" በሚል ዘይቤ የሠራተኛውን ማህበር መሪዎች ለማባረር የፈፀሙትን አድሃሪ ድርጊት አጥብቆ ያወግዛል::

ሐ/ <u>የገበሬ ማሕበራት፤</u>

ደርግ አሁን በሚከተለው ፖለቲካ የተነሳ በተለይም ከአድሃሪው ቢሮክራሲና ከአድርባይ ድርጅቶች ጋር ባደረገው ህብረት ምክንያት ሰፊው የኢትዮጵያ አርሶ አደር በፀኑ እየተሰቃየ ነው::

በንጉሡ ሚኒስቴር በአከፋፋይና በመጋዘን ድርጅቶች ውስጥ የተሰገሰጉትን ቀንደኛ ቢሮክራቶች ሴራና አሻጥር ለመቋቋም ገበሬው አቋቁሞአቸው የነበረት የህብረት ሱቆች በመፈራረስና የቢሮክራሲው ተቀጥላ እየሆኑ በመሄድ ዓላማቸውን ፍፁም ስተዋል:: በዚህም ምክንያት ለገበሬው ለዕለት ተለት ኑሮ የሚያስፈልጉት ሸቀጣ ሸቀጦች በባለገሩ ፈጽሞ አይገኙም ለማለት ይቻላል::



ሰፊው አርሶ አደር ህዝብ ለአብዮት ጥበቃ ከመሀሉ የመለመላቸው አርሶ አደሮች ወታደራዊ ትምህርት ከሰለጠኑ በኋላ ወደተመለመሉበት አካባቢ ተመልሰው እንዲያገለግሉት ሲጠይቅ ደርግ ይህን ጥያቄ በማንአለብኝነት በመሻር የደቡብን ወደሰሜን፤ የሰሜኑን ወደ ደቡብ እያዘመተ ነው:: የብሄረሰቦች መብት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ አለመፈታት አብዮታችንን አስጊ ሁኔታ ላይ እየጣለ እያለ ይህ የደርግ እርምጃ የሚጠቅመው በብሄረሰቦች መሀል ያለውን ቅራኔ ለማባባስ ብቻ ነው::

የኢትዮጵያ አርሶ አደር የመደብ ጠላቶቹን በማያዳግም ሁኔታ ለመደምሰስ ተደራጅቶ ለመጨረሻው ፍልሚያ መዘጋጀት ይኖርበታል:: ይህንኑ በመገንዘብ ህቡዕ ተራማጆች ከብዙ ዓመታት ጀምሮ ለዚሁ አብዮታዊ ዓላማ ታግለዋል፡ተሰውተዋልም:: ከብዙ ትግል በኋላ የተገኘው ድል ማለት የየካቲት 25ቱ የመሬት አዋጅ ገበሬውን ለማንቃት ለማደራጀትና ለማስታጠቅ አመቺ ሁኔታን ስለፈጠረ፤ ታጋዮች ባደረጉት መራራ ትግልና ቅስቀሳ የገበሬው የንቃት የድርጅትና የትጥቅ ጉዳይ ከቀድሞ የካቲት 66 አንድ እርምጃ ወደፊት ሄዶ ነበር ለማለት ይቻላል:: ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ያለው የኢት.ሁኔታ የሚያሳየን ገበሬውን ለማንቃት ለማደራጀት ለማስታጠቅ የሚደረገው ትግል እየከሰመ መሄዱን ነው:: በሰሜን ኢትዮጵያ የገበሬ ማኀበራት አሉ ለማለት ያስቸግራል:: በደቡብና በደቡብ ምዕራብ ያሉት እየፈራረሱ፤ያልፈራረሱትም ወደመንግስት አካልነት እየተለወጡ ናቸው::

ይህንን ፀረ አብዮት ድርጊት በቆራጥነት የሚታገሉ ታጋይ የገበሬ ማኀበራት መሪዎች በአስተዳደሩና "በኢማሌድህ"አባል ድርጅቶች /ወዝ፤ ሰደድና ማሌሪድ/ "ቀኝ መንገደኛ" በሚል ስም እየተጨፈጨፉ እየታሰሩና እየተሰደዱ ናቸው:: መንግስቱና አድርባዮች ገበሬው ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የመረጣቸውን መሪዎችን እየሻሩ የራሳቸውን ወኪሎች ከላይ በማስቀመጥ ላይ ናቸው::

ይህ ጉባዔ ይህንን ፀረ ህዝብ ድርጊት ማለት ጭፍጨፋና ሹም ሽር በጥብቅ እያወገዘ ታጋይ ገበሬዎች የድርጅታቸውን ህዝባዊና ዲሞክራሲያዊ ህልውና ለመጠበቅ የሚያደርጉትን ትግል ከምን ጊዜውም በበለጠ እንዲያፋፍሙ ሀይላቸውንም ከህቡዕ ተራማጆች ጋር እንዲያስተባብሩ አብዮታዊ ጥሪ ያደርጋል::

በሚያዝያ 1970 ዓ.ም. መ.ኢ.ገ.ማ. /መላው ኢትዮ. የገበሬዎች ማኅበር/ ተቋቋሟል:: ለዚሁ ድርጅት መቋቋም ህቡዕ ታጋዮች ከፍተኛ ትግል እንዳደረጉ ብዙ መስዋዕት እንደከፈሉበት የታወቀ ነው:: ስለዚህም የመኢገማን መቋቋም ተራማጆች እንደአንድ ድል ይቆጥሩታል::

ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ መንግስት ይህንን ድርጅት መሳሪያ ሊያደርገው ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው:: ድርጅታዊ ህልውናውንና ዲሞክራሲያዊ አርምጃውን በቁጥጥሩ ስር በማድረግ ላይ ነው:: የመኢገማን ፣ ሠ.አ.ኮ. "ያማከሯችሁ" በማለት ወዛደር መሳፍንትን እየሰገሰገበት ነው::

ቢሆንም ታጋይ ገበሬዎችና ሀቀኛ ተራማጆች ድርጅቱ አሁንም ዲሞክራሲያዊ አሰራር እንዲኖረው፣ ነፃነቱ እንዲጠበቅ ከፍተኛ ትግል እያካሄዱ ናቸው:: በዚህም ትግላቸው ምክንያት "ቀኝ መንገደኛ" በመባል እየተረሸኑ እየታሰሩና እየተሰደዱ ናቸው:: ይህ ጉባዔ የነዚህን ታጋዮች ትግል ያለምንም ማወላወል እየደገፈ የሚደረግባቸውን ማናቸውም ተፅዕኖ በጥብቅ ያወግዛል:: ያጋልጣል፣ ይታገላል:: በወህኒ የታጐሩት በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል::

ሠ/ የመምህራን ማህበር/ሮች/፣

በ1967/68 ዓ.ም. የመምህራን ማኅበራትን አመራር ኢ.ህ.አ.ፓ በቁጥጥሩ ሥር አውሎት ስለነበር፣ በጊዜው ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት አብዮታዊ ትንተና በማድረግ ፈንታ የኢህአፓን ደብዳና ፖሊሲ ብቻ በማስተጋባት ተወስኖ ነበር:: በኋላም በውስጡ በተነሳው ውዝግብ ፍርክስክሱ ወጥቶ ማህበራዊ ሚናው ወደማክተሙ ተቃርቦ እንደነበር ይታወሳል::

ሆኖም በ1968 ዓ.ም. መጨረሻ ላይ ታጋይ መምህራን በራሳቸው አነሳሽነትና በሀቀኛ ተራማጆች ድጋፍ ነፃና ዲሞክራሲያዊ ማኅበር ለማቋቋም ከፍተኛ ተጋድሎ አድርገዋል: ትግሉም ፍሬ በመስጠቱ ማህበሩ ሀቀኛ መስመር በመያዝ ላይ ሳሉ ደርግና የቀኝ አድርባዮች እንደገና አፈራርሰዋቸው በምትካቸው ፀረ ዲሞክራቲክ በሆነ መንገድ አድርባዮችንና አገብጋጆችን በማደራጀት ላይ ናቸው::

ይህ ጉባዔ ይህንን ሁኔታ ከመረመረ በኋላ ለአብዮታዊ መምህራን ማህበር መመስረት ሲታገሉ የነበሩና አሁንም በወህኒ የታጐሩ ታጋይ መምህራን ባስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል::

የመምህራን ማኅበር አብዮታዊ አመራር ማግኘት ለነገዪቱ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ገንቢ ካድሬዎችን ለማዘጋጀት ዋስትና በመሆኑ ታጋይ መምህራን ይህንን ትግላቸውን በታላቅ ጥንቃቄና በትጋት እንዲያጋፋበት አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል:: ለዚህም ከጎናቸው የተሰለፈ መሆኑን ያረጋግጣል::



ሠ/ የከተማ የቀበሌ ማህበራት፣

በሀምሌ 19 ቀን 1967 ዓ.ም. በታወጀውና የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤቶችን በመንግስት ቁጥጥር ስር ባዋለው አዋጅ መሠረት ሰፊውን የከተማ ደሀ ህዝብ በየቀበሌው ለማደራጀት ተችሏል:: የቀበሌ ማኅበራት ይህንን አብዮታዊ አዋጅ ለመጠበቅና በስራ ላይ ለማዋል ብቻ ሳይሆን አብዮታውያን ወጣቶችና ጭቁን ሴቶች በነዚህ ማኅበራት አካባቢ እንዲደራጁ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል:: የቀበሌ ማህበራት የህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ባህሪ ነበራቸውና ሰፊው የከተማ ደሀ ህዝብ ለአብዮቱ የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ከፍ እንዲል ረድተውታል::

ህዝቡ በቀበሌ ማኅበራት ተደራጅቶ ያደርግ የነበረውን አብዮታዊ አስተዋጽኦ የተገነዘቡትና በድርጊትም ያዩት የደነገፈው ንዑስ ከበርቴ ቡድን/ኢ.ህ.አ.ፓ/ ነፍሰ ገዳዮች ብዙ የቀበሌ ማኅበራት መሪዎችን የሠ.አ. ኮሚቴና የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴ አባሎችን በመረሸን በነዚህ ማኅበራት ላይ ይህ ነው የማይባል ግፍና በደል ፈጽመዋል:: ይህንን ጥቃት በቆራጥነት ተቋቁመው ወደፊት በመራመድ ላይ እንዳሉ፣ አሁን ደግሞ ደርግ ቢሮክራሲና አድርባዮች በፈጠሩት ህብረት ሌላ ታላቅ ተፅዕኖ እየተደረገባቸው ነው::

በአሁኑ ወቅት የቀበሌ ማኅበራት ህዝባዊ ድርጅቶች መሆናቸው ቀርቶ ወደፋሺዝም መንግስታዊ አካል እየተለወጡና የህዝቡ መገልገያ መሳሪያዎች መሆናቸው ቀርቶ የመጨቆኛ መሳሪያዎች እየሆኑ ሄደዋል:: በህዝቡ ላይ የተጫኑ እንጂ የህዝቡ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች መሆናቸው እያከተመ በመሄዱ ላይ ነው:: በዚህም ምክንያት በቀበሌና በሰፊው ሕዝብ መካከል ያሉት ቅራኔዎች እየከረሩና እየሰፉ በመምጣት ላይ ናቸው:: ደርግና አድርባዮች የሾሟቸውን የቀበሌ መሪዎች ህዝቡ ስለሚፈራ በድርጊታቸውም ስለሚጠላቸው ያለው አብዮታዊ ተሳትፎው በተመልካችነት ደረጃ ብቻ ተወስኗል::

ምንም እንኳን ደርግና አድርባዮች በቀበሌ ማኅበራት ላይ የሚያደርጉት ተፅዕኖ አላይ እንደዘረዘርነው ከባድና አስከፊ ቢሆንም ሀቀኛ ታጋዮች አሁንም የቀበሌዎችን ዲሞክራሲያዊ ባህሪ ለመጠበቅ ከፍተኛ ትግል እያደረጉ ነው:: በዚህም ትግላቸው "ቀኝ መንገደኛ" በሚል ክስ እየተባረሩ እየታሰሩና እየተሰደዱ ናቸው:: ማኅበራችን ይህንን ድርጊት በፅኑ እያወገዘ የታሰሩት ባስቸኳይ እንዲፈቱ የሚደረግባቸውም ማናቸውም ተፅዕኖ እሁኑኑ እንዲቆም አጥብቆ ይጠይቃል:: ለዚህም ያለምንም መቆጠብ ይታገላል::

## 9. የተራማጆች ህብረት ጥያቄና የወዛደሩ ፓርቲ፤

የኢትዮጵያ አብዮት ከፈነዳበት ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ ሀቀኛ የሆነ የተራማጆች ህብረት መመስረት አስፈላጊና መሠረታዊ ጥያቄ መሆኑን በማመን ማህበራችን ያለማቋረጥ ታግሏል፡፡ ይታገላልም፡፡ ተራማጆች ሰፊውን ጭቁን ሕዝብ ከዳር እስከዳር ለማንቃት፣ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ ብሎም በጠላቶች ላይ እንደአንድ ሰው ሆኖ እንዲነሳ ለማድረግ ሀላፊነት አለባቸው ለዚህም ሀቀኛ የሆነ የተራማጆች ህብረት ለመመሥረትና ለአብዮቱ አመራር ለመስጠት፣ ተራማጆች በአብዮቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ስምምነት መድረስ፣ እነዚህንም ስምምነት የተደረሰባቸውን ነጥቦች በሥራ እንዲተረጎሙ ጊዜና ሁኔታ በማይፈታው ታታሪነት ከግራና ከቀኝ አድርባይነት በመወገድ አብዮቱን ለሚያጋጥሙት ችግሮች በጋራ ታክቲክ መቀየስና መፍትሄ ለመስጠት መቻል አለባቸው፡፡

ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮት የደረሰበትን የትግል ደረጃ ስንገመግም የኢትዮጵያ ተራማጆች ለዚህ አጣዳፊ ጥያቄ መመሥረት መታገልና ለወዛደሩ ፓርቲ መሠረት ሊሆን የሚችል ህብረት ለመጣል ሀቀኛና አብዮታዊ በሆነ የዲሞክራሲ ዘዴ በጋራ ትግል ሲያካሄዱ ብቻ መሆኑን ማህበራችን ያምናል፡፡ ታሪክም እንደሚያሳየን የወዛደሩን ፓርቲ ለመመስረት የሚችለውን ህብረት ለመጣል፣ የማይተዋወቁ የማርክሲስት ሌኒኒስት የጥናት ክበቦች ወይም ድርጅቶች በውስጥ ጋዜጦቻቸው አማካይነት ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥና የሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ርዕዮተ ዓለም ለማስፋፋት በወዛደሩና በሰፊው ህዝብ መካከል ትግል ለማካሄድ በጋራ ነፃ ጋዜጣ ማውጣትና በተለይም የወዛደሩ መደብ በንዑስ ከበርቴው ርዕዮተ ዓለም እንዳይበረዝ፣ የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ ትግል ማካሄድ ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ የርዕዮተ ዓለምና የፖለቲካ ትግል በኋላ በአንድ የጠራ የማሌ መስመር ላይ የሚመሠረተው ሀቀኛ የወዛደር ፓርቲ ይሆናል፡፡ እንግዲህ ይህን እያመለከተን ዛሬ በአንድ በኩል ለብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም በተግባር እንዲተረጎም በሚታገሉ አብዮታውያንና በሌላ በኩል ይህንን ፕሮግራም በስፋ ተቀብለው በተግባር እንዳይተረጎም ሰዩ ሰዩ አሻጥሮችን በሚሠሩ የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች /ሰደድ፣ ወዝና ማሌሪድ/ ያለው ልዩነት ለእውነተኛው የወዛደር ፓርቲ መመሥረት በሚታገሉ ማሌዎችና ለንዑስ ከበርቴ ፓርቲ በሚታገሉ ድርጅቶች መሀከል የሚካሄድ የመደብ ትግል ነው፡፡

በመሆኑም ከሰፊው ህዝብ ጀርባ የሚቆም በዲሞክራሲና ሀቀኛ በሆነ አብዮታዊ፣ ትግል ያልተገነባ የንዑስ ከበርቴ ፓርቲ በምንም አይነት የወዛደሩን የበላይነት የሚያስፍንና የሰፊውን ህዝብ ጥቅም የሚጠብቅ ሳይሆን፣ በሰፊው ሕዝብ ጫንቃ ላይ ቁጭ የሚል ፈላጭ ቆራጭ ፓርቲ ይሆናል፡፡



ስለዚህም ማህበራችን ይህንን የንዑስ ከበርቴዎችንና የቢሮክራቶችን ጥቅም የሚያንፀባርቅ ፓርቲ መመሥረት የሚጣደፉ ቀኝ አድርባዮችን /ሰደድ፣ ወዝና ማሌሪድ/ ከአብዮታውያንና ከሰፊው ሕዝብ ጎን በመሆን እየታገለ፣ ለሀቀኛ የተራማጆች ህብረት መመሥረት ያልተቋረጠ ጥረት ያደርጋል፡፡ ለዚህም ዓላማ በቆራጥነት ከሚጥሩ አብዮታውያን ጎን ይሰለፋል፡፡

## 10/ ስለ ዲሞክራሲ፤

ከቀድሞ የካቲት ሆነ የየካቲት አብዮት ከፈነዳ በኋላ የኢትዮጵያ አብዮታውያንና ጭቁን ሕዝቦች አንግበው ከወጡት መፈክር አንዱ የዲሞክራሲ ጥያቄ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከየካቲት 66 አብዮት በኋላም ሰፊው ሕዝብ በመጠኑም ቢሆን የተቀዳጃቸው የዲሞክራሲ መብቶች በየጊዜው የተቀበረትን የፀረ አብዮት ሴራዎች እንዲቋቋም ረድተውታል፡፡ ለአብዮቱ ትግል መፋጠን የዲሞክራሲ አስፈላጊነት በመገንዘብ የዲሞክራሲ መብቶችን በአስቸኳይ መለቀቅ እንዳለባቸው በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ በማያሻማ ሁኔታ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ሰፊው ህዝብ በንቃት በድርጅትና በትጥቅ ጉዳና እየተጓዘ በአብዮታዊ አመጽ ሥልጣንን ይቀዳጅ ይችል ዘንድ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ መለቀቅ ዐቢይ ጥያቄ ይሆናል፡፡

ነገር ግን ጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ ይህንን ለአብዮቱ ዋስትና የሆነውንና ደግሞ ደጋግሞ በሰፊው ሕዝብ ፊት የገባውን ቃል ኪዳን በመሻሩ ዛሬ ሀገሪቱና አብዮቱ በተለያ ውጥረት ላይ እንዲገኙ አድርጓል፡፡ ማህበራችን ከዚህ በፊት ለሰፊው ህዝብ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች እንደታገለ ሁሉ ዛሬም ለዚሁ የአብዮቱ ዕምብርት ለሆነው ጥያቄ ከሚታገሉ የማሌ ድርጅቶች፣ ዲሞክራቶችና ሀገር ወዳዶች ጎን በመሰለፍ ከሁለት ዓመት በፊት በህዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ረቂቁ እነለማየሁ ኃይሌ አፍነውት ነበር የተባለው የዲሞክራሲን መብት በስራ ላይ ለማዋል የተሰናዳው ረቂቅ አሁኑኑ በሥራ ላይ እንዲውል አጥብቆ ይታገላል፡፡

የዲሞክራሲ መብቶችን አጣዳፊ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ፣

ሀ/ የሰፊው ህዝብ ለንቃት፣ ለድርጅት የሚያደርገውን ትግል በይበልጥ እንዲያፋፍምና ከዳር እስከዳር እንደአንድ ሰው ሆኖ በመነሳት በጠላቶች ላይ በማያዳግም ሁኔታ ድል እንዲቀዳጅ በር ስለሚከፍት፣ ብሎም ከውጭ የሚመጣበትን ወረራ ለመቋቋምና የእናት ሀገሩን ክብር፣ ብሔራዊ ነፃነትና ሀልውና ለማስጠበቅ እንዲችል፣

ለ/ አድኃሪው ቢሮክራሲው የሚሸርበበትን ሴራና የኢኮኖሚ አሻጥሮች ነቅቶ እንዲጠባበቅና ሴራውን ለማጋለጥ እንዲችል፣

ሐ/ በአብዮቱ ውስጥ የተፈጠሩ ህዝባዊ ድርጅቶች የፖለቲካ ህልውና እንዲጠበቅና

በድርጅቶች መሀከል የሚፈጠረውን ቅራኔ ለማስወገድና የሰፊውን ሕዝብ ተሳትፎ በይበልጥ ለማፋፋም እንዲሁም ህዝባዊ ድርጅቶችና የቢሮክራሲው አውታሮች ተፋጠው በሚገኙበት አካባቢ ሕዝባዊ ድርጅቶች በአሸናፊነት እንዲወጡ የሚደረገውን ትግል ለማፋፋም፣

መ/ በሶሻል ማለትም በትምህርት፣ በጤና ጥበቃና እንዲሁም በሌሎች የሶሻል ዘርፎች የተፈጠሩትን ችግሮች ሰፊው ሕዝብ በጋራ እንዲወጣቸው ለማድረግ፣

ሠ/ ህቁና የሆነ የተራማጆች ህብረት እንዲመሠረት በተራማጆች መሀከል የጠራ የርዕዮተ ዓለም ትግል እንዲካሄድ ለማድረግና፣ የወዝ አደሩን ፓርቲ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩንና አብዮታዊ ሠራዊቱን ለመመሥረት አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር፣

ረ/ ዛሬ አብዮቱ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ በሚገኝበት ሰዓት በህዝባዊ ድርጅቶች መሀከል፣ በተራማጆች በንግድ ከበርቴውና በመንግሥት፣ በብሔረሰቦችና በመንግሥ[ት] መሀከል በአፋጣኝ በመስፋት ላይ ያሉ ቅራኔዎችን ለማጥበብና በጠቅላላው ሀገሪቱ የገባችበትን ከሪዝ ለመውጣት የዲሞክራሲ መብቶች አሁኑኑ መለቀቅ አፋጣኝና አንገብጋቢ ነው:: ስለሆነም በአሊቶማ ዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ የሚለውን የራሱ መፈክር በማድረግ ለዚሁ መፈክር አሁኑኑ በሥራ መዋል ከሚታገሉ አብዮታውያንና ሰፊው ህዝብ ጎን ቆሞ በቁራጥነት ይታገላል::

በመጨረሻም ለጠንካራ ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር አስፈላጊ የሆኑትና የተቋቋሙት ሕዝባዊ ድርጅቶች በዲሞክራሲ መነፈግ ምክንያት እየጠወለጉ የደርግና የአድኃሪው ቢሮክራሲ ህብረት መሣሪያ እየሆኑ በመሄዳቸው ይህንን አዝማሚያ ለመቋቋም ለሚያስችሉትና አብዮታችን አሁን ካለበት ውጥረት ለመውጣት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱት የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ እንዲለቀቁ ይታገሉ ዘንድ ማህበራችን አብዮታዊ ጥሪ ያቀርባል::

11. ስለቢሮክራሲ፣

ከቀደሞ የፊውዳል ቡርዣ ሥርዓት የተወረሰው አድኃሪው ቢሮክራሲ የፊ'ዳሊ ዝምና'ኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም ለመጠበቂያ ሆኖ ብሎ በኢምፔሪያሊስቶች ተኮትኩቶ ያደገና በቀጥታ ጥቅሙ ከነዚሁ የለየላቸው የሰፊው ህዝብ ጠላቶች ጋር በሺህ ድሮች የተሳሰረ በ[መ]ሆኑ ባለው የኃይሎች አሰላለፍ ከፀረ አብዮቱ ሰፈር የሚመደብ ነው:: ስለሆነም ይህ



የፀረ አብዮት ኃይል ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር አብሮ መመታት እንዳለበት በብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ላይ ቁልጭ ብሎ ሠፍሯል:: ይህ'ፀረ ሕዝብ መዋቅር የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታቸውን ካፈነዱበት ጊዜ አንስቶ አብዮቱን ለማዳፈን ይህ ነው የማይባል ሴራዎችን እንደሠራና እንደሚሠራ ለማንም ግልጽ ነው:: በውስጥና በውጭ የሚቀነባበሩ ፀረ አብዮት ሴራዎች ተሸካሚ በመሆኑም ሰፊው ሕዝብ በገዛ አብዮቱ ላይ እንዲነሳ የተቀነባበረ የፓለቲካና የኢኮኖሚ አሻጥሮች ፈጽሟል:: በአብዮቱ ወቅት የተፈጠሩትን ሕዝባዊ ድርጅቶች እንዳያድጉ በማፈን፣ በተራማጆች መሀከል ቅራኔ በመፍጠርና ሠርጎ በመግባት በአብዮቱ ሠፈር ይህ ነው የማይባል ጉዳትን አስከትሏል:: በሰሜንና በደቡብ ምሥራቅ አዝማች ሆኖ በፈጸመው አሻጥር ለሀገሪቱ ከበር መደፈሪያና ለብዙ ጭቁን ሕዝቦች ሕይወት መጥፋት ተጠያቂ ነው::

ዛሬ አብዮቱ በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ በሚገኝበት ወቅት'በሰፊው ሕዝብና በቢሮክራሲው መሀከል የሚካሄደው የሞትና የሽረት ትግል ከመቼውም ይበልጥ ተፋፍሞ የሚገኘው እላይ በጠቀስናቸው ምክንያቶች ነው::'ነገር ግን የጊ.ወ.ደርግ በአመራር ሚናው ባሳየው ከፍተኛ የመወላወል ጠባይ በሚሊተሪና በሲቪል ቁልፍ የአስተዳደር ቦታዎችን ይዞው ቢሮክራሲው እንዲይዝ አድርጓል::

የአሊቶማ 185ው ጠ/ጉባዔ የኢትዮጵያን ሁኔታ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከመረመረና ካጠና በኋላ ዛሬ አብዮቱ ከቀበበሳ አፋፍ ላይ ሊድን የሚችለው ይኸው አድኃሪ ቢሮክራሲ ካላንዳች ርህራሄ መመታት ሲችል ብቻ መሆኑን ያምናል::

በአፍ ሳይሆን በድርጊት ይኸው የሚሊተሪና የሲቪል ቢሮክራሲ እንዲደመሰስ ከሚታገሉ የሰፊው ሕዝብና አብዮታውያን ጎን ቆሞ ያለውን የትግል አንድነት እየገለጸ፣

አድኃሪ ቢሮክራቶች ከያዙት ቁልፍ ቦታዎች እየተነሱ በምትካቸው ተራማጆችና፣ ሀገር ወዳዶች እንዲተኩ፣

የሰፊው ሕዝብ የሥልጣን አውታር የሆኑት ህዝባዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩና ከቢሮክራሲው ተጽዕኖ እንዲላቀቁ፣

በአንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ሠርጎ በመግባት የህቁና ተራማጆች ህብረት እንዳይፈጠር ከደርግ ቀኝ ክንፍና ከአድርባዮች ጋር በመሆን በመኢሶንና እንዲሁም በሌሎች ህቁና ተራማጆችና ሀገር ወዳጆች ላይ የሚነዛውን ውዥንብርና የሚፈጸሙውን የመግደል የማፈንና የማሰር ወንጀል በአስቸኳይ እንዲቆም ለማድረግ ፣

ሰፊው ሕዝብ የሚያካሄደው የፀረ ቢሮክራሲ ትግል እንዲፋፋም የሰፊው ሕዝብ ነፃ አብዮታዊ እርምጃዎች እንዲለቀቁ፣

የቢሮክራሲው ማጥፊያ የሆነውን የዲሞክራሲን መብቶች መለቀቅ የሚቃወሙትን የአፍ ፀረ ቢሮክራቶች በገቢር ግን የቢሮክራሲው "ሰርጎ ገቦች" የሆኑትን ቀኝ አድርባዮች ለማጋለጥ ማህበራችን በቁራጥነት ይታገላል::

## 12. ስለ ኢኮኖሚ፣

ኢትዮጵያ ባለፉት 5 ዓመታት ከአብዮቱ ሂደት ጋር የሚመጣጠን የካፒታል ኢንቬስትመንት ባለማግኘትዋና በበዙ የፖሊሲና የአሠራር ጉድለቶች የተነሳ ቢቢ ሮክራሲውና በአንዳንድ ፀረ ህዝብ ከበርቴዎች አሻጥር በአድሃሪው የሶማሌ ወረራ ምክንያት በከፍተኛ የኢኮኖሚ አዘቅት ውስጥ ተገኛለች::

በዚህም ቀውስ የተነሳ ፋብሪካዎች የንግድና መገናኛ ድርጅቶች ቀድሞ ከነበረበት ሁኔታ አጅግ ቀንሰው ይገኛሉ::በገጠርም አጅግ በተሰበጣጠሩ ምክንያቶች የተነሳ ዘንድሮ በትግራይና በሰሜን ሸዋ ከሚሊዮን በላይ የሚሆን ደሃ ገበሬ በረሃብ አለንጋ በመገረፍ ላይ ይገኛል:: እንዲሁም የአንበጣ መንጋ በሀገሪቱ ክፍለ ሃገር በመንሠራፋቱ በችግሮች ላይ ችግር ተፈጥሯል:: በአድሃሪው የሶማሌ ጦር የተነሳ በደቡብ ምሥራቅና በምሥራቅ ገበሬዎች ላይ በደረሰው ጉዳት የዚህ አካባቢ ህዝቦች አጅግ ከፍተኛ ችግር ውስጥ ገብተዋል:: በተጨማሪም ባጠቃላይ አገሪቱዋ ውስጥ ያለው የትራንስፖ ርት ችግሮች የሸቀጣሸቀጦች መጥፋት የዋጋ መናር፣ ለኑሮ የሚያስፈልጉት ዓይነት እንጀራ፣ አንጨት፣ ጨውና ዘይት፣ ሳሙናና ልብስ በቀላሉ ባለመገኘታቸው በአንፃሩም የዋጋ ሚዛን 20/ በመቀነሱ ወዛአደሩና ሌላው የህብረተሰብ ክፍል በኑሮው ውድነት ወደፊት ሊገፋበት አልቻለም::

ሆኖም ይህ ሁሉ ትርምስ እያለ መንግሥት አፋጣኝና አስፈላጊ እርምጃዎች ከመውሰድ ይልቅ " በአብዮት ጊዜ የተለመደ ነውና " ቻለው በማለት ለችግሮቹ መፍትሄ ከመ ስጠት ተቆጥቧል:: ስለሆነም የአብዮቱ አንገብጋቢ ጥያቄዎች እስከአሁን ድረስና የአጭር ጊዜ የኢኮኖሚ ፕላን እስኪወጣ ድረስ " በአብዮት ጊዜ የተለመደ ነው" ብቻ በማለት ችግሮቹ እንደማይወገዱና እንዲያውም ለፀረ አብዮት ሀይሎች እንደሚያመቹ ማህበራችን ያምናል:: ሃገሪቱን ከምትገኝበት አዘቅት ለማውጣት ተገቢ የሆኑትን ርምጃዎች ለመውሰድ የሚደረጉትን ጥረቶች ማህበራችን ይደግፋል::

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፤

የወያኔ ገቶና ፣ ከውስጥ ሆና ቦርቦር ለማዳከም ያደረገው ሙከራ ስላሳተካከለት እርሱን ከገቶና ቶያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከተርበ ጊዜ ጀምሮ፣ከአስር ዓመት በላይ በሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ያለማቋረጥ ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግሉ ሲያካሂድ በኖረው ማህበራችንና በነዚህም አስር ዓመታት ያለተከታታይ ነፃነት በመገመት የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግሉ ሲያስተጋቡ በኖረት ፲ከ የተናወም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መ ካ ከሻ ሆነው በቆየት በታጠቅና በተገለጸን ስም መጠቀም ጀምረዋል፡፡ የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም ታጠቅና ተገለጸን በ14. ዓመት ቆራጥ ትግሉ ባተረፈት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው፡፡እንዲሁም ከውስጥ ሆና ያታለውን የኢትዮጵያ ተማሪያችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆና ወሬገበር በመንዛት ለማፋፋም ነው፡፡ይህም እንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው፡፡ ለማገናዘብ፣የተለመደው የመጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያዘ፣የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር አባልነትን የሚያመለከት ገን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንደታወቁልን እንድታስታውቁልን እንጠይቃለን፡፡ለእነዚህ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው ''ዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን'' በሚባል ስም የታወቀው የነ አሰፋወሰን — ወንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው፡፡

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአሊተማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ